# የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ

## (የተማአአዕ)








# የትኩረት ቡድን የመስክ ስራ የትግበራ መመሪያ

## /ለ3ኛ ጊዜ የተሻሻለ ዕትም/

**ህዳር 2018 ዓ.ም**

**<u>ባህር ዳር</u>**

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

1. መግቢያ ..... 3
2. ዳራ /Background/ ..... 4
3. የመስክ ስራ የትግበራ ዓላማዎች፡ ..... 9
4. የመስክ ስራ ትግበራው መሠረታዊ መርሆዎች ..... 10
5. ለትኩረት ቡድኖች የመስክ ሥራ ፕሮግራም ..... 10
6. የትኩረት ቡድኖች የዕቅድ ዝግጅት መመሪያ ..... 14
7. ቴክኒካዊ መረጃዎች (Techinical Data) ..... 52
8. የአገግ መሳሪያዎች /PRA TOOLS/ ..... 74

## ምስጋና

የተቀናጀ ማህበረሰብ ዓቀፍ አሳታፊ ዕቅድ ዓላማ ህብረተሰቡ በአካባቢው የሚገኙ የልማት መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም እና እንቅፋቶችን በመለየት የአሳታፊ ዕቅድ አስተቃቀድ ዘዴን በክልላችን ተግባራዊ ማድረግ ነው። ይህ የየሴክተሮች የትኩረት ቡድን የመስክ ስራ የትግበራ መመሪያ ማሰልጠኛ ሰነድ የተዘጋጀው በታንዛኒያ ሀገር ከተገኘው ልምድ በመነሳት በትግራይ ክልል ተግባራዊ ሆኖ ውጤት ስለተገኘበት ይህን ተሞክሮ ከግምት ውስጥ በማስገባት ወደ አማራ ክልል በማምጣት አሳታፊ የአስተቃቀድ ዘዴውን ተግባራዊ ለማድረግ የተጀመረ ነዉ፡፡

የትኩረት ቡድን የመስክ ስራ የትግበራ መመሪያን ለማዘጋጀት የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት እና ባለፉት ዓመታት ይህ ስራ በክልሉ እንዲጀመር ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ያልተቋረጠ የመዋእለ ንዋይ እና የቴክኒክ ድጋፍ ሲያበረክት ለነበረው **ዩኒሴፍ** /UNICEF/ እንዲሁም **ሔልቬታስ ኢትዮጵያ የአማራ አካባቢያዊ አስተዳደር ፕሮጀክት** በክልሉ ባሉ የተወሰኑ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ስራውን በማስቀጠል እያበረከተ ላለው የመዋእለ ንዋይ እና የቴክኒክ ድጋፍ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕላንና ልማት ቢሮ ልዩ ምስጋና ያቀርባል፡፡

# 1. መግቢያ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት በግልጽ እንዳስቀመጠው የአካባቢ አስተዳደሮች የተሰጣቸውን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ተጠቅመው ህብረተሰቡን በማነቃነቅ፣ የህዝቡን ተሳትፎና የውሳኔ ሰጪነት ሚናን በማጐልበት፣ በሰው ኃይል፣ በበጀትና በአሠራር ራሳቸውን በማጠናከር ለልማቱ መፋጠንና ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ በሚያስችል መልኩ እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በክልሉ ያልተማከለ አስተዳደርን ከማስፈን አንጻር ከክልል እስከ ወረዳ የቀበሌን መዋቅር ጨምሮ ተግባርና ሃላፊነታቸውን ለይቶ አስቀምጧል፡፡ ያልተማከለ አስተዳደርን ለማጠናከርና ስር እንዲሰድ ለማድረግ በክልሉ መንግስት ይህን የሚመለከት አዋጅ ፀድቆ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ በዚህም አዋጅ ስለ አጠቃላይ ዕቅድ ሂደት ከመግለጹም በላይ ህብረተሰቡን በቀጥታ ከእቅድ ዝግጅት እስከ ግምገማ ያሉት ሂደቶች ላይ ማሳተፍ፣ ማብቃት እና የባለቤትነት ስሜት መፍጠር አስፈላጊነት ተገልጿል፡፡ ይህም ያልተማከለ አስተዳደር ዓላማ ተደርገው ከተቀመጡት ውስጥ አንዱ የሆነውን የህብረተሰብ ተሳትፎ እና ማብቃት የሚለውን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ ሚና ከመጫወቱም በላይ ለአሳታፊ ዕቅድ ሂደት ህጋዊ መሰረት ይጥላል፡፡

የክልላችን ያለፉት ዓመታት የዕቅድ ሂደት ሲታይ የመካከለኛ ጊዜ እና የአጭር ጊዜ እቅድ እየተዘጋጀ ተግባራዊ ሲደረግ የቆየ ሲሆን አሁንም በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም የዕቅድ ሂደት ከዝግጅት ጀምሮ ሲታይ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና የልማት እቅዶች መሰረት ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ ሆኖም የዕቅድ ሂደቱ ከላይ ወደታች የዕቅድ አዘገጃጀት ዘይቤ ላይ ይበልጥ ያተኮረ በመሆኑ ከታች ወደ ላይ የእቅድ አዘገጃጀት ዘይቤን በመተግበር አሁን ያለውን የዕቅድ ሂደት ወደ ላቀ እና ውጤታማ ደረጃ ማድረስ እጅግ ወሳኝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ እቅድ(የተማአአዕ) (Integrated Community Based Participatory Planning-ICBPP)ን በመተግበር የህብረተሰቡን ተሳትፎ በልማት እና በመልካም አስተዳደር ግንባታ ውስጥ መሰረት በማስያዝ የላቀ ተጠቃሚ ከማድረጉም በላይ ያልተማከለ አስተዳደርን እውን ለማድረግ አይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

ይህን ዕውን ከማድረግ አንፃርም የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ በክልሉ ምክር ቤት አዋጅ መሰረት የህግ ሰውነት አግኝቶ ራሱን የቻለ የክልል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ መቋቋሙ

ይታወቃል። ቢሮው ከሀገሪቱ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ጋር በተቀናጀ መልኩ ክልል አቀፍ የእድገት ማዕቀፍን መሰረት በማድረግ የክልሉን የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅድ በማዘጋጀት ዕቅዱ በትክክል ለመተግበሩ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ክትትልና ግምገማ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

ስለሆነም በክልላችን የተማአአዕን /ICBPP/ን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችል ይህ የየሴክተሮች የትኩረት ቡድን የመስክ ስራ የትግበራ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. ዳራ /Background/

የአማራ ክልል መንግስት የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችል ዩኒሴፍን/UNICEF/ ድጋፍ በመጠየቅ የቴክኒክ እና የመዋለ ንዋይ እገዛ ለማግኘት ተችሎ የነበር ሲሆን ስራውንም በይፋ ለማስጀመር እንዲያግዝ ከክልል እና ከተመረጡ 3 ወረዳዎች የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በዚህም መነሻነት በክልሉ በየደረጃው ባሉት የመንግስት መዋቅር የአብይ /Steering/ እና የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲዋቀር በማድረግ ስራው እንዲጀምር ተደርጎ ነበር፡፡ ከክልል እና ከወረዳ የተውጣጣ የኮሚቴዎቹ አባላት ከትግራይ ክልላዊ መንግስት ሰፋ ያለ ፕሮግራም ተይዞ ተሞክሮ እንዲቀስሙ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ የክልሉ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በዩኒሴፍ /UNICEF/ አስተባባሪነት ለ 5 ቀናት የተዘጋጀ የአሰልጣኞች ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

በቀበሌ ደረጃ ለሚዘጋጀው የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር የሚያግዙ ይህንን የአሰልጣኞች የሥልጠና ማኑዋል ጨምሮ ብዛታቸው 11 ጥራዝ የሚሆኑ የመስክ ትግበራ መመሪያዎች የትርጉም ሥራ በቀድሞው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ተጠናቆ የህትመት ሥራው በዩኒሴፍ በኩል በበቂ ኮፒ እንዲታተም ተደርጎ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ ለሚገኙ ሴክተር መ/ቤቶች ባለሙያዎች እንዲሁም ለህብረተሰብ ተወካዮች እንዲሰራጭ በማድረግ ወደ ትገበራ ተግብቶ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጅ በመስክ ከተደረገው ክትትልና ድጋፍ፣ ከምክክር መድረኮች፣ ከዕቅድ ባለሙያዎች ዕይታ፣ **ሔልቬታስ ኢትዮጵያ የአማራ አካባቢያዊ አስተዳደር ፕሮጀክት** አስተባሪዎችና ባለሙያዎች ከተሰጠ አስተያየት እንዲሁም ካለው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ሰነዱን ለ3ኛ ጊዜ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሰነዱ ተሻሽሎ ቀርቧል፡፡

በመሆኑም በማሰልጠኛ ማኑዋሉ እና በየሴክተሮች የትኩረት ቡድን የመስክ ስራ የትግበራ መመሪያ ውስጥ በዋናነት የተደረጉ ማሻሻያዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

◈ ከአደረጃጀት አኳያ፡ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ማሳየት እንዲቻል በወረዳ እና በክልል ደረጃ ግልጽ የሆነ የአብይ ኮሚቴና የቴክኒክ ኮሚቴ መቀመጡ፣

◈ በቀበሌና በወረዳ መካከል ግልጽ የሆነ የዕቅድና የሪፖርት ቅብብሎሽ መቀመጡ፣

◈ ከዚህ ቀደም የነበረው የትኩረት ቡድኖች አደረጃጀት ለስራ አመች ሆኖ ባለመገኘቱ አደረጃጀቱን እንደገና ለማስተካከል ተችሏል፡፡ ስለሆነም በአዲስ የተሻሻለው የትኩረት ቡድን አወቃቀር የመንግስት አደረጃጀትን /የልማት ቡድኖችን/ የተከተለ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህም አሰራሩ በመንግስት ዘንድ ይበልጥ ትኩረት እንዲያገኝና ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የህጻናት ጉዳይ በዕቅድ ውስጥ መካተት ስላለበት የህጻናት ተወካዮች በየትኩረት ቡድኖች ውስጥ የሚሳተፉበት አግባብ ተፈጥሯል፡፡

◈ በአሰልጣኞች የስልጠና ማኑዋል ውስጥ ይታዩ የነበሩ አላስፈላጊ ድግግሞሾች እንዲወጡ በማድረግ ማኑዋሉ ለስልጠና አመች እንዲሆን ተደርጓል፡፡

◈ በመጀመሪያው ክለሳ በ10ሩ የትኩረት ቡድን የትግበራ ማኑዋሎች ውስጥ ይታይ የነበረውን አላስፈላጊ ድግግሞሽ በማስወገድ እና በተለያዩ ሰነዶች ተዘጋጅተው የነበሩትን አሰራሮች አሰባስቦ በአንድ ዶክመንት ብቻ በማጠቃለል እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ይህም ቀደም ሲል የነበረውን ስራውን አክብዶ የማየት ሁኔታ አስወግዷል፡፡ ለአሰራርም ምቹና ቀላል እንዲሆን አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የህጻናት የትኩረት ቡድን እንዲካተት ተደርጎ ወደ 11 የትኩረት ቡድን እንዲያድግ ተደርጎ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ለ3ኛ ጊዜ በተደረገ ክለሳ 2 የትኩረት ቡድን ማለትም ገቢና ወጪ እንዲሁም ድህነትና አካባቢ የሚሉት በሌሎች ቡድኖች እንደሚሰሩ ታሳቢ በመደረጉ ተቀንሰው የትኩረት ቡድኑ ብዛት 9 ሆኗል፡፡

◈ ይህ የመስክ ትግበራ መመሪያ የተቀናጀ ማህበረሰብ ዓቀፍ አሳታፊ ዕቅድን በታችኛው የመንግስት መዋቀር እና በማህበረሰቡ ዘንድ በተገቢው መልኩ ለመተግበር ያመች ዘንድ የተዘጋጀ መሳሪያ ነው፡፡ መመሪያውም በመስክ ስራ ወቅት በየደረጃው የሚገኙ አወያዮች (አመቻቾች) ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እና ተግባርና ኃላፊነታቸውን አውቀው በሚገባ ማህበረሰቡን በማወያየት ዕቅዱን እንዲያዘጋጁ የሚያግዝ ሰነድ ነው፡፡ ሰነዱም የሚከተሉትን ዘርፎች ማለትም 1. ግብርና እና ተፈጥሮ ሀብት፣ 2. የማህበረሰብ ጤና፣ 3. ትምህርት፣ 4. ንፁህ መጠጥ ውሃና የአካባቢ ንጽህና፣ 5. መልካም አስተዳደር፣ 6. መንግድ፣ 7. ሴቶችና ስርዓተ ፆታ፣ 8. ወጣቶች እንዲሁም 9. የህጻናት የትኩረት ቡድንን ያካተተ ነው።

## የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ የትግበራ መዋቅራዊ አደረጃጀት

**በቀበሌ ደረጃ**

የትኩረት ቡድን የሚያካትታቸው በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ የአባወራና እማወራ እንዲሁም የሴቶች የልማት ቡድን መሪዎች፣ ከ8-10 አባላት ከህጻናት ፓርላማ ወይም ከት/ቤት እና ከት/ቤት ውጭ የሚወከሉ ህጻናት፣ የአካል ጉዳተኞች ተወካዮች

- መልካም አጋጣሚዎችን ለልማት መለየት
- በቀበሌ ደረጃ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡትን መልካም ዕድሎችን መዘርዘር
- መረጃን መሰብሰብ (በአባወራ/እማወራ እና በትናንሽ መንደሮች ደረጃ)

የቀበሌ የተማአአዕ አመቻች ቡድን (16-17)

1.የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ
2. 7 ቀበሌ ላይ ከሚገኙ የመንግስት ሠራተኞች /የግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ፣ የጤና ባለሙያ፣ የት/ቤቱ ርዕሰ መምህር፣ የቀበሌው ስራ አስኪያጅ፣ የእንሰሳት ባለሙያ፣ የሲቪክስ መምህር እና ፖሊስ/
3. 6 ተወካዮች (2 ከወጣት፣ 2 ከሴቶችና 2 ከአርሶ አደር) ከእነዚህ አንዱ/ዷ የሴቶችና ህጻናት ተወካይ ወይም የማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት ተወካይ
4. የወረዳ አመቻቾች 2
5. መያድ ተወካይ 1/ካለ/

- የተለዩትን መልካም አጋጣሚዎች ከልማት ሥራዎች ጋር ማጣጣም፣ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡትን መለየት፣
- መልካም አጋጣሚዎችን ለመጠቀም እንቅፋት የሆኑትን መለየት፣
- የእንቅፋቶችን መንስኤዎች እና የሚያስከትሉትን ችግሮች መተንተን፣
- ለተለዩት እንቅፋቶች የመፍትሄ ርምጃዎችን ማስቀመጥ፣
- ከመሪዎች፣ ከተቋሞች እና ከትኩረት ቡድኖች የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን ማጠናከር፣
- የቀበሌ ማህበረሰብ ልማት ዕቅድ ማዘጋጀት

**በወረዳ ደረጃ**

የወረዳ የተማአአዕ ኮሚቴዎች ቡድን፡-

1. የወረዳ ዓብይ ኮሚቴ
2. የወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ

**ፕላንና ልማት**

የሴክተር ዕቅድ በማቀናጀት የተጠቃለለ የወረዳ ዕቅድ ያዘጋጃል

የወረዳ ምክርቤት፡-

የወረዳውን ዕቅድ ማጽደቅ

## በወረዳ ደረጃ የአብይና የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት

### የወረዳ አብይ ኮሚቴ አባላት

1. የፕላን እና ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ………………..……………….......…….. ሰብሳቢ
2. የአስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ……………………..………………....……….…ጸኃፊ
3. የገንዘብ ጽ/ቤት ኃላፊ………….……………………..……..……………... አባል
4. የትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ………………………………………..………….አባል
5. የጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ………..……………………..….…..…………..….አባል
6. የግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ………………………………………......…….….አባል
7. የመሬት ጽ/ቤት ኃላፊ..……………………….…………..………………አባል
8. የውሃ እና ኢነርጅ ጽ/ቤት ኃላፊ……………..........................................…….…..አባል
9. የሴቶች ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ ……………..…………አባል
10. የሠላምና ጸጥታ ጽ/ቤት ኃላፊ…..……………………………………………አባል
11. የመንገድ ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ጽ/ቤት ኃላፊ………………………አባል
12. የአካባቢና ደን ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ……………………………………………አባል
13. የሥራና ክህሎት ኃላፊ /በከተማ/፣ የህብረት ስራ ጽ/ቤት ኃላፊ/በገጠር/……አባል
14. እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ተቋማትም ሊካተቱ ይችላሉ

### የወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት

1. ከፕላንና ልማት የፕላን ዝግጅት ቡድን መሪ ……………………….. ሰብሳቢ
2. በቡድን አባላቱ የሚመረጥ ሴክተር ባለሙያ………………….……… ጸሐፊ
3. ከገንዘብ ጽ/ቤት 1 ባለሙያ …………………………..…….….……..አባል

4. ከትምህርት ጽ/ቤት 1 ባለሙያ……………………………………...……አባል

5. ከጤና ጥበቃ ጽ/ቤት 1 ባለሙያ…………………….……………..……አባል

6. ከግብርና ጽ/ቤት 1 ባለሙያ ……………………………….……………..አባል

7. ከመሬት ጽ/ቤት 1 ባለሙያ…………..........................................…………አባል

8. ከውሃ እና ኢነርጅ ጽ/ቤት 1 ባለሙያ…………………….………...….አባል

9. ከሴቶች ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ጉዳይ ጽ/ቤት 1 ባለሙያ…….…አባል

10. ከሠላምና ጸጥታ ጽ/ቤት 1 ባለሙያ…………………………………….አባል

11. ከመንገድ ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ጽ/ቤት 1 ባለሙ………………አባል

12. ከአካባቢና ደን ጥበቃ ጽ/ቤት 1 ባለሙያ ……………………………..አባል

13. ከሥራና ክህሎት 1 ባለሙያ /በከተማ/፣ ከህብረት ስራ ጽ/ቤት 1 ባለሙያ /በገጠር/…………………..………………………………………………..አባል

14. እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ተቋማትም በአባልነት ሊካተቱ ይችላሉ

**የትኩረት ቡድን**

የትኩረት ቡድን ማለት በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ ሁሉም የአባወራና እማወራ የልማት ቡድን ሰብሳቢዎች፣ ሁሉም የሴቶች የልማት ቡድን ሰብሳቢዎች፣ እንዲሁም የአካል ጉዳተኞች ተወካዮችን ያካተተ ሆኖ በዕድሜ፣ በፆታ እና በንዑስ ቀበሌ ስብጥር እንዲሳተፉ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከ8-10 አባላት ያሉት 1 የትኩረት ቡድን ከህጻናት ፓርላማ ወይም ከት/ቤት እና ከት/ቤት ውጭ የሚወከሉ ይሆናል፡፡ የትኩረት ቡድኑ የሚዋቀረው በየተማአአዕ አመቻቾች በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት ሲሆን እያንዳንዱ የትኩረት ቡድን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል። የህፃናት ጉዳይ በህጻናት የትኩረት ቡድን መልካም አጋጣሚዎችና ዕንቅፋቶች ከተለዩ በኋላ በስምንቱም የትኩረት ቡድኖች ዕቅድ ውስጥ ተካቶ መታቀድ ይኖርበታል። የአንድ የትኩረት ቡድን አባላት ብዛት ቢያንስ ከ8-10 መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጅ ከላይ በተቀመጠው መልኩ የተመረጡ የትኩረት ቡድን አባላት ቁጥር ከ8 በታች ከሆነ የቀበሌውን ልማት ያውቃሉ ተብለው የሚታሰቡ ተጨማሪ አባላት በማህበረሰቡ ተመርጠው የትኩረት ቡድኑ አባል መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 3. የመስክ ስራ የትግበራ ዓላማዎች፡

የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ እቅድ ሂደት በክልል ደረጃ በማስረጽ ህብረተሰቡን በልማት እና በመልካም አስተዳደር ስራዎች በቀጥታ ለማሳተፍና ለማብቃት ሲሆን የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

እነዚህም፡-

- በክልል እና በወረዳ ደረጃ ለሚተገበሩት የልማት ፕሮጀክቶች ወይም ተግባራት ላይ ሚና ላላቸው የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የአሳታፊ ዕቅድ ዝግጅት አማራጭ መሳሪያዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል፡፡
- የስርአተ ጾታ ጉዳይን በተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ ማካተት የሚያስችል አመቺ ወይም ሁነኛ መሳሪያ ለመፍጠር፡
- በእያንዳንዱ የልማት ስራ እንቅስቃሴ ዉስጥ የማህበረሰቡን መሰረታዊ ፍላጎቶች እና የስርአተ ጾታ ተኮር ጉዳዮችን ትኩረት የሚያሻቸው መሆኑን ሊያረጋግጥ የሚያስችል ስርዓት ስራ ላይ ለማዋል፡
- በሁሉም የማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ እቅድ ሂደት ደረጃዎች ዉስጥ የማህበረሰቡ ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ያካተተ መሆኑን ለማረጋገጥ ማስቻል ናቸዉ፡፡

## 4. የመስክ ስራ ትግበራው መሠረታዊ መርሆዎች

ይህንን የመስክ መመሪያ ለማዘጋጀት በሥራ ላይ የዋለው መርህ ትኩረቱ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ እቅድን በክልል እና በወረዳ ደረጃ ለሚገኙ የልማት ተግባሪዎች እና ተባባሪዎች ቀላል እና ለመረዳት በሚያመች መልኩ ለማዘጋጀት እንዲችሉ ማድረግ ነዉ፡፡ በመርህ ደረጃም የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ ተሣትፎአዊ እቅድ ዝግጅት ተግባራትን የበለጠ አሣታፊ እና ማህበረሰብ አቀፍ ማድረግ ነው፡፡ የመስክ መመሪያውም እስከአሁን በስራ ላይ የዋሉትን የተለያዩ የእቅድ ዝግጅት መሳሪያዎች ቁጥር እንዲቀንስ እና ጥራቱን በማስጠበቅ በመደበኛነት ለተለያዩ አሳታፊ እቅድ ዝግጅት ስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ ነዉ፡፡

**መርሆዎች፡**

- በየደረጃዉ ለሚገኙ የልማት ተግባሪዎች እና ፈጻሚዎች ቀላልና ለመረዳት የሚያመች ዕቅድ ማዘጋጀት (Less Complicated)፣
- ይበልጥ አሳታፊ ዕቅድ ማድረግ (More Participatory Plan)፣
- ማህበረሰብ ዓቀፍ (Community Based)፣
- የእቅድ ዝግጅት መሳሪያዎች ቁጥር እንዲቀንስ ማድረግ (Standardizes & Reduces the Number of Planning tools) የሚሉት ናቸው፡፡

# 5. ለትኩረት ቡድኖች የመስክ ሥራ ፕሮግራም

| በመጀመሪያው ቀን የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት |
|---|

1. ከሁሉም የቀበሌ ነዋሪዎች ጋር የማህበረሰብ ስብሰባ በማካሄድ በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ ሁሉም የአባወራና እማወራ የልማት ቡድን ሰብሳቢዎች እንዲሁም ሁሉም የሴቶች የልማት ቡድን ሰብሳቢዎች የቀበሌውን የተማአእዕ እንሚያዘጋጁ በማህበረሰቡ በኩል ውክልና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከ8-10 አባላት ከሀጻናት ፓርላማ ወይም ከት/ቤት እና ከት/ቤት ውጭ የሚወከሉ ሆነው 1 የትኩረት ቡድን ሆነው በዕቅዱ ይሳተፋሉ፡፡ እንዲሁም የአካል ጉዳተኞችን ማሳተፍ ተገቢ ነው፡፡ የአንድ የትኩረት ቡድን አባላት ብዛት ከ8-10 መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጅ ከላይ በተቀመጠው መልኩ የተመረጡ የትኩረት ቡድን አባላት ቁጥር ከ8 በታች ከሆነ የቀበሌውን ልማት ያውቃሉ ተብለው የሚታሰቡ ተጨማሪ አባላት

በማህበረሰቡ ተመርጠው የትኩረት ቡድኑ አባል መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከ10 በላይ ከሆኑ ደግሞ የተሻለ ግንዛቤ ያላቸውን በመምረጥ 10 እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

2. በቀበሌው የተወከሉት የልማት ቡድን ሰብሳቢዎችና የህጻናት ተወካዮች እርስ በእርሳቸው እንዲገናኙና እንዲተዋወቁ ማድረግ፣

3. የቡድኑን የአሰራር ሂደት፣ ደረጃዎች እና ቁልፍ ትርጉሞች ማስተዋወቅ፣

4. አመቻቾች ለተወከለው የዕቅድ ዝግጅት ቡድን የክልሉን እና የወረዳውን የልማት ዓላማዎችና ግቦች ማስተዋወቅ፣

5. የተመረጠው የዕቅድ ዝግጅት ቡድን በ9 የትኩረት ቡድኖች ከተከፋፈለ በኋላ በቀበሌ ደረጃ ያሉትን የእየዘርፉን መልካም አጋጣሚዎች፣ እንቅፋቶችና መንስኤዎቻቸውን ይለያል፣

6. በቀበሌ ደረጃ የተለዩትን መልካም አጋጣሚዎች እንደጠቀሜታቸው በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣

7. የእየዘርፉን /1. ግብርና እና ተፈጥሮ ሀብት፣ 2. የማህበረሰብ ጤና፣ 3. ትምህርት፣ 4. ንፁህ መጠጥ ውሃና የአካባቢ ንጽህና፣ 5. መልካም አስተዳደር፣ 6. መንገድ፣ 7. ሴቶችና ስርዓተ ፆታ፣ 8. ወጣቶች እንዲሁም 9. የህጻናትን መረጃዎች ማሰባሰብ፣

## በ 2ኛዉ ቀን በመስክ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

8. የአሳታፊ የገጠር ግምገማ ወይም አገግ /PRA/

8.1 የግብርና እና ተፈጥሮ ሀብት የትኩረት ቡድን የቀበሌውን ወቅታዊ የጊዜ መቁጠሪያ ሰሌዳ /Seasonal calendar/ እና የአዝማሚያ ማሳያ መስመር /Trend Line/ እንዲሁም የቀበሌውን ማህበረሰብ የሀብት ደረጃ /Wealth Ranking/ እንዲሁም የቀበሌውን የስርዓተ ፆታ ሀብት ካርታ /Gender Resource Map/እንዲጠቀም ማድረግ፣

8.2 የማህበረሰብ ጤና የትኩረት ቡድን የቀበሌውን ወቅታዊ የጊዜ መቁጠሪያ ሰሌዳ እና የአዝማሚያ ማሳያ መስመር /Trend Line/ እንዲጠቀም ማድረግ፣

8.3 የትምህርት የትኩረት ቡድን የማህበረሰቡን የካርታ ንድፍ /Community Sketch Map/ እና የአዝማሚያ ማሳያ መስመር /Trend Line/ እንዲጠቀም ማድረግ፣

8.4 ውሃ እና የአካባቢ ንጽህና የትኩረት ቡድን የአካባቢ የቅኝት ጉዞን /Transect Walk/ እንዲጠቀም ማድረግ፣

8.5 የመልካም አስተዳደር የትኩረት ቡድን የቀበሌውን የተቋማት ትንተና /Institutional Analysis/፣ የቀበሌውን ማህበረሰብ የሀብት ደረጃ /Wealth Ranking/ እንዲሁም የቀበሌውን የስርዓተ ፆታ ሀብት ካርታ /Gender Resource Map/ እንዲጠቀም ማድረግ፣

8.6 የመንገድ የትኩረት ቡድን የቀበሌውን ታሪካዊ የጊዜ ማሳያ መስመር /Historical Timeline/ እንዲጠቀም ማድረግ፣

8.7 የሴቶችና የስርዓተ ፆታ ጉዳዮች የትኩረት ቡድን የቀበሌውን የስርዓተ ፆታ ሀብት ካርታ /Gender Resource Map/ እና ስርዓተ ፆታን መሰረት ያደረገ የየዕለት ተግባራት የጊዜ መቁጠሪያ (Daily Activity Calander by Gender) እንዲጠቀም ማድረግ፣

8.8 የወጣቶች የትኩረት ቡድን የቀበሌውን ታሪካዊ የጊዜ ማሳያ መስመር /Historical Timeline/፣ የቀበሌውን ወቅታዊ የጊዜ መቁጠሪያ ሰሌዳ እንዲጠቀም ማድረግ እንዲሁም የቀበሌውን ማህበረሰብ የሀብት ደረጃ /Wealth Ranking

8.9 የህጻናት የትኩረት ቡድን የቀበሌውን የተቋማት ትንተና /Institutional Analysis/ እንዲጠቀም ማድረግ፣

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- አንዱ የትኩረት ቡድን ያዘጋጀውን ሌላው የትኩረት ቡድን ለራሱ ስራ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገው በምሳሌነት ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

9. የቀበሌዉን የልማት ግቦች መወሰን፣

10. የቀበሌውን የልማት ግቦች ለማሳካት የመፍትሄ ርምጃወችን መወሰን፣

11. የትግበራ ቅደም ተከተሎችን ወይንም ዝርዝር ተግባራትን መለየት

**በ 3ኛዉ ቀን በመስክ የሚከናወኑ ስራዎች እና ተግባራት**

12. የታቀዱ ተግባራትን ለመፈጸም የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን፣ ሀብቶችንና ቁሳቁሶችን መለየት

13. ለግብዓቶች፣ ለሀብቶች እና ለቁሳቁሶች የወጪ ግምት ማስቀመጥ፣

14. ትግበራውን ቅደም ተከተል ለማስያዝ የሚያስፈልጉ የቅድሚያ መስጫ ነጥቦችን መወሰን፡

15. ውጤቶችን ለመለካት የሚያስችሉ የለውጥ አመልካቾችን ማዘጋጀት፡

**በ 4ኛዉ ቀን በመስክ የሚከናወኑ ስራዎች እና ተግባራት**

16. የቀበሌዉን የእየዘርፍ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ እቅድ ዝግጅት ስራ ማጠናቀቅ፣

17. በእየዘርፉ የተጠናቀቀውን የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ ረቂቅ ሰነድ ወደ አንድ በማጠቃለል የቀበሌው የዕቅድ ሰነድ አድርጎ ማዘጋጀት፣

## በ 5ኛዉ ቀን በመስክ የሚከናወኑ ስራዎች እና ተግባራት

18. የተዘጋጀውን የቀበሌ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ ለቀበሌው ነዋሪዎች ለውይይት በማቅረብ በዒላማዎች፣ ግቦች፣ ዓላማዎች፣ መልካም አጋጣሚዎች፣ እንቅፋቶችና መንስኤዎች፣ ሊወሰዱ በሚገባቸው የመፍትሄ ርምጃዎች፣ የትግበራ ደረጃዎች፣ ግብዓቶች፣ ወጪዎች፣ ቅድሚያ የሚሹ ተግባራት ደረጃዎች እና አመልካቾች ላይ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ፣

19. ከአምስተኛው ቀን በኋላ፡-

- የተዘጋጀውን የቀበሌ የተማአአፅ በ3 ቅጅ በማዘጋጀት በ3 ቀናት ውስጥ 1 ቅጅ ለቀበሌው፣ 1 ቅጅ ለወረዳ አስተዳደር እና 1 ቅጅ ለወረዳው ለፕላንና ልማት ማቅረብ፣
- ከዚህ በተጨማሪም ቀበሌ ላይ ያሉ የየሴክተሩ ተወካዮች የየራሳቸውን ዕቅድ በወረዳ ደረጃ ላሉ እናት ሴክተሮች መላክ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ሁሉም በወረዳ ደረጃ ያሉ የሴክተር ጽ/ቤቶ በየቀበሌው በተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ መርህ የተዘጋጀውን የየራሳቸውን ሴክተር ድርሻ ቀበሌዎች ለወረዳ አስተዳደር ከላኩት የዕቅድ ሰነድ ላይ በመውሰድ ወረዳዊ የየሴክተር ዕቅድ በማዘጋጀት ለወረዳው ፕላንና ልማት መላክ ይኖርባቸዋል፡፡
- ከወረዳው በሚሰጠው  አስተያየት መሰረት ዕቅዱን ማዳበር

## 6. የትኩረት ቡድኖች የዕቅድ ዝግጅት መመሪያ

### በመጀመሪያው ቀን

በመጀመሪያዉ ቀን የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ ዝግጅት ስራ የሚጀምረዉ የቀበሌዉን ነዋሪዎች በማሰባሰብ ስለ ዕቅዱ ሂደት በሰፊው ማስተዋወቅ ነው፡፡ በስብሰባው ላይ የሚሰሩት ስራዎች እንደሚከተለዉ ይሆናሉ፡፡

1. የተማአአዕ አመቻቾች የቀበሌውን አባወራዎች/እማወራዎች መረጃ ቅጽ ሰብስበው በትክክል መሞላቱን ያረጋግጣሉ፤

2. በማህበረሰቡ ስብሰባ ላይ በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ ሁሉም የአባወራና እማወራ የልማት ህብረት ሰብሳቢዎች እንዲሁም ሁሉም የሴቶች የልማት ህብረት ሰብሳቢዎች የቀበሌውን የተማአአዕ እንሚያዘጋጁ በማህበረሰቡ በኩል ውክልና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከህጻናት ፓርላማ ወይም ከትምህርት ቤት እና ከት/ቤት ውጭ ከ8-10 አባላት በመሆን 1 የትኩረት ቡድን ሆነው ይመረጣሉ፡፡ በሌላ በኩልም የአካል ጉዳተኞች ተወካዮች እንዲሳተፉ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ይህ ቡድን ከቀበሌው አመራር ጋር በመሆንና ከየተማአአዕ አመቻቾች ጋር በመተባበር በቀበሌው የዕቅድ ዝግጅት ሂደት ተባብረው ይሰራሉ።

3. የተመረጡት የልማት ህብረት ሰብሳቢዎች በፆታና በዕድሜ ስብጥር በትኩረት ቡድኖች ይደራጃሉ፤ የአካል ጉዳተኞች ተወካዮችም ቢቻል በእያንዳንዱ የትኩረት ቡድን ውስጥ መካተት ይገባቸዋል፡፡

### ሀ. የስብሰባው አካሄድ ቅደም ተከተል

- የቀበሌው ዋና አስተዳደሪ ስብሰባውን ይመራል፡፡
- ሁሉም የሚመለከታቸው የቀበሌው ነዋሪዎች በማህበረሰብ ስብሰባው ላይ መሳተፍ አለባቸው፡፡
- የቀበሌው ዋና አስተዳደሪ፣ የተማአአዕ አመቻቾች፣ የቀበሌ አመራሮች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ይጋብዛል፡፡

• ዋና አስተዳደሪው የስብሰባውን ዓላማ ይገልጻል። ይህ የሚከናወነው በጋራ የተጻፈውን ደብዳቤ በማንበብ ይሆናል።

• የተማአአዕ አመቻቾች ቀደም ሲል ስምምነት ላይ የተደረሰበትን የዕቅድ ዝግጅት የጊዜ ሰሌዳ ለተሰብሳቢው ያስተዋውቃሉ፡፡

• ቀጥሎ የስብሰባው ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን ወይም ጥያቄዎችን እንዲያቀርቡ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡

• ሁሉም ተሳታፊዎች እኩል ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው፡፡ በተለይም ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የዕድሜ ባለጸጎች፣ ህጻናት፣ ልዩ ፍላጎት የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ ወዘተ፤ እኩል ዕድል በማግኘት የየራሳቸውን ሃሳብ ስለመስጠታቸው እርግጠኛ መሆን ይገባል፡፡

## ለ. ስለትኩረት ቡድኖች መታወቅ የሚገባቸው ነጥቦች

1. በቀበሌው የሚካሄዱ ውይይቶች በትኩረት ቡድኖች አማካይነት ይሆናል።
2. የትኩረት ቡድኑ የሚዋቀረው በየተማአአዕ አመቻቾች በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት ነው። እያንዳንዱ የትኩረት ቡድን የሚከተሉትን አባላት ይኖሩታል።

• በቀበሌው ውስጥ ውክልና የተሰጣቸው የልማት ህብረት ሰብሳቢዎችና ህጻናት በ10 የትኩረት ቡድን ውስጥ በተመጣጠነ የዕድሜና የፆታ ስብጥር ይመደባሉ፡፡

3. የተማአአዕ አመቻቾች በየትኩረት ቡድኑ የተመደቡት አባላት እርስ በእርስ እንዲተዋወቁ ካደረጉ በኋላ በመቀጠል የትኩረት ቡድኖች የየራሳቸውን ሰብሳቢ እንዲመርጡ ያደርጋሉ።
4. ከየተማአአዕ አመቻቾች አንዱ ለውይይት ቡድኑ አባላት ስለ አጠቃላይ ጉዳዮች ምን እንደሚሰራ እና እንዴት እንደሚሰሩ ከዚህ በታች የተቀመጠውን ጽሁፍ ያብራራል፡፡

## ሐ. የሚሰሩትን ተግባራትና ቁልፍ ትርጉሞች ማስተዋወቅ

የተማአአዕ ትግበራ አዲስ የሆነ የአሳታፊ ዕቅድ ዝግጅት ፅንሰ ሀሳብ ሲሆን የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡-

1. የሚከተሉትን አሳታፊ ሁኔታዎች (Participatory tools) ይጠቀማል፡፡ እነዚህም

- የማህበረሰብ ስብሰባ (Community Meeting)፣
- የአካባቢው ንድፍ ካርታ (Community Sketch Map)፣
- የቅኝት ጉዞ (Transect Walk)፣
- ታሪካዊ የጊዜ መስመር ማሳያ (Historical timelines)፣

- ወቅታዊ የጊዜ መቁጠሪያ (seasonal Calander)፣
- የተቋማት ትንተና (Institutional analysis)፣
- ስርዓተ ፆታን መሰረት ያደረገ የየዕለት ተግባራት የጊዜ መቁጠሪያ (Daily Activity Calander by Gender)፣
- የስርዓተ ፆታ ሀብት ካርታ /Gender Resource Map/
- የእማወራዎች/አባወራዎች የሃብት ደረጃ መስጠት (Household wealth Ranking)፣
- የትኩረት ቡድን ውይይት (Focus Group Discussion) እና
- የገቢ ምንጮች እና ወጪዎችን መለየት (Identification of ource of Income & expenditure)፡፡

2. የአስተቃቀድ ስነ-ዘዴው ማህበረሰቡ በአካባቢው የሚገኘውን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የልማት እንቅፋቶችን መፍታት የሚያስችል ነው።
3. ማህበረሰቡ ያለውን ሃብት እንዲያውቅ እና እነዚህን ሃብቶች እንዴት አድርጎ ለላቀ ጥቅም ማዋል እንደሚቻል ያግዛል፡፡ በተያያዘም ማህበረሰቡ በራስ የመተመመን ስሜትን ያዳብራል።
4. የአስተቃቀድ ሂደቱም የክልሉን ርዕይ፣ ፖሊሲ እና ስትራቴጂዎች እንዲሁም የወቅቱን የአኻጋሪ ዕድገትና ዘላቂ የልማት ዕቅድ መሰረት ያደርጋል፡
5. የተማአአዕ ሂደት ውጤቱ የድርጊት መርሃግብር ሣይሆን በቀበሌ ደረጃ የተጠቃለለ ዕቅድ ነው፡

## መልካም አጋጣሚዎች

መልካም አጋጣሚዎች ማለት ማህበረሰቡ ሊጠቀምባቸው የሚችል በማህበረሰቡ ውስጥ ወይም ከማህበረሰቡ ውጪ ያሉ ሀብቶች ማለት ነው። መልካም አጋጣሚዎች እንደሚከተለው ይከፈላሉ፡-

1. **ማህበረሰቡ ያለው እና በአግባቡ እየተጠቀመበት ያለ ሃብት**፤ ለምሳሌ፣

- **ግብርና እና ተፈጥሮ ሀብትን በተመለከተ፡** የእንስሳት ህክምና አገልግሎት/የእንስሳት ጤና ኬላ/ በመኖሩ መጠቀም መቻላቸው፣ የቤት እንሰሳትና ከፍተኛ ዋጋ ሊያወጡ የሚችሉ የሰብል ምርቶች መኖራቸውና በአግባቡ መጠቀም መቻሉ፡
- **የማህበረሰብ ጤናን በተመለከተ፡** በአካባቢው የሚገኙ የጤና ተቋማት በመኖራቸው መጠቀም መቻላቸው፡

▪ **ትምህርትን በተመለከተ፡** በአከባቢዉ የሚገኙ የትምህርት ተቋማት (ቅድመ መደበኛ፣ የመዋለ ህጻናት ትምህርት ቤት እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) በመኖሩ መጠቀም መቻላቸዉ፡፡

▪ **ውሃ እና የአካባቢ ንጽህናን በተመለከተ፡** በአካባቢው የሚገኙ የውሃ ተቋማት /የወንዝ ውሃ፣ ምንጭ፣ የእጅ ጉድጓድ፣ መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ/ በመኖራቸው መጠቀም መቻላቸው፡

▪ **መልካም አስተዳደርን በተመለከተ፡** የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት በአካባቢው መኖርና በአግባቡ መጠቀም መቻል፡ ገቢና ወጪን በተመለከተ በአካባቢው የሚገኙ የገንዘብ አበዳሪ ተቋማትን በአግባቡ መጠቀም፡

▪ **መንገድን በተመለከተ፡** በአካባቢ የሚገኙ መንገዶችን በአግባቡ መጠቀም፡

▪ ምርቶች መኖራቸውና በአግባቡ መጠቀም መቻሉ፡

▪ **ሴቶችና የስርዓተ ፆታ ጉዳይን በተመለከተ፡** ትንንሽ እንሰሳትንና የምግብ ሰብል ዝርያዎችን በአግባቡ መጠቀም፡

▪ **ወጣቶችን በተመለከተ፡** ስራን ለመፍጠር የሚያስችሉ እንደ ብድር፣ ገበያና ለሽያጭ የሚውሉ ምርቶች መኖርና በአግባቡ መጠቀም መቻል፣

▪ **ህጻናትን በተመለከተ፡** በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ለህጻናት ምቹ የመጫዎቻ መገልገያ ዕቃዎች መኖር፡

2. **ማህበረሰቡ ያለው እና በአግባቡ ያልተጠቀመበት ሀብት** ምሳሌ፡

▪ **ግብርና እና ተፈጥሮ ሀብትን በተመለከተ፡** ለመስኖ ልማት የሚውል መሬት እንዲሁም የከርሰ ምድርና የገጸ ምድር ውሃ በአካባቢው ቢኖርም በአግባቡ ጥቅም ላይ አለማወል፡ ለእርሻ ሊውል የሚችል መሬት ቢኖርም በአግባቡ ጥቅም ላይ አለመዋሉ፡ ገቢና ወጪን በተመለከተ ለቡና ምርት ሊውል የሚችል መሬት እያለ ነገር ግን በአግባቡ ጥቅም ላይ አለመዋል፡

▪ **የማህበረሰብ ጤናን በተመለከተ፡** በአካባቢው የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ቢኖሩም በአግባቡ ጥቅም ላይ አለመዋላቸው፡

▪ **ትምህርትን በተመለከተ፡** በአሁኑ ጊዜ በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ያሉ የመማሪያ ክፍሎችን ለጎልማሶች ትምህርት ሊዉሉ ማድረግ የሚቻል ቢሆንም ግን አለመጠቀም፡፡

▪ **ውሃ እና የአካባቢ ንጽህናን በተመለከተ፡** የውሃ ተቋማት በአካባቢው ቢኖሩም ያለመንከባከብና በአግባቡ መጠቀም አለመቻል፡

▪ **መልካም አስተዳደርን በተመለከተ፡** የፍትህ ተቋማት ቢኖሩም በአግባቡ መጠቀም አለመቻል፡

▪ **መንገድን በተመለከተ፡** የመስኖ አገልግሎት ተቋማት ቢኖሩም በአግባቡ መጠቀም አለመቻል፡

- **ሴቶችና የስርዓተ ፆታ ጉዳይን በተመለከተ**፡ የተለያዩ የግቢ ማስገኛ ዕድሎች ቢኖሩም በአግባቡ አለመጠቀም፡
- **ወጣቶችን በተመለከተ**፡ የእርሻ መሬቶች ቢኖሩም በሙሉ አቅም አለመጠቀም፡
- **ህጻናትን በተመለከተ**፡ በአካባቢው ለህጻናት መዋያ እና መጫዎቻ ሊሆን የሚችል ሜዳ እያለ በአግባቡ አለመያዝ፡ የህጻናት ክትባት እየተሰጠ በአግባቡ አለመጠቀም፣ ወዘተ....

3. **ማህበረሰቡ ያለው እና ሙሉ በሙሉ/ምንም/ ያልተጠቀመበት ሀብት**፡- ምሳሌ፡

- ግብርና እና ተፈጥሮ ሀብትን በተመለከተ፡ ለሩዝ ሰብል ልማት ተስማሚ የሆነ መሬት በአካባቢው ቢኖርም በጭራሽ ማምረት አለመቻል፡ የዝናብ ውሃ በብዛት ያለ ቢሆንም አሰባስቦ ጥቅም ላይ አለማዋል፡ ገቢና ወጪን በተመለከተ ለጣውላ ምርት ሊውል የሚችል ደን እያለ አለመጠቀም፡
- የማህበረሰብ ጤናን በተመለከተ፡ ለጤና ተቋማት ግንባታ የሚውሉ የግንባታ ቁሳቁሶች በአካባቢው እያሉ ጭራሽ አለመጠቀም፡
- **ትምህርትን በተመለከተ፡** የትምህርት ቤት ግንባታ ቁሳቁሶች በአከባቢዉ እያለ ግንባታ በማድረግ ስራ ላይ ያለማዋል፡፡
- **ውሃ እና የአካባቢ ንጽህናን በተመለከተ፡** ለውሃ ተቋማት ግንባታ የሚውሉ የግንባታ ቁሳቁሶች በአካባቢው እያሉ ጭራሽ አለመጠቀም፡
- **መልካም አስተዳደርን በተመለከተ**፡ ያለዕድሜ ጋብቻን የሚከለክል ህግ ቢኖርም ህጉን ተጠቅሞ ማስቀረት አለመቻል፡
- **መንገድን በተመለከተ**፡ በአካባቢው ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎች ያሉ ቢሆንም ምንም አለመጠቀም፡
- **ሴቶችና የስርዓተ ፆታ ጉዳይን በተመለከተ**፡ እንደ ደንጋይ፣ አሸዋ፣ ወዘተ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ቢኖሩም ምንም አለመጠቀም፡
- **ወጣቶች በተመለከተ**፡ እንደ ደንጋይ፣ አሸዋ፣ ወዘተ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ቢኖሩም ምንም አለመጠቀም፡
- **ህጻናትን በተመለከተ**፡ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የመጻዳጃ ቤት እያለ ነገር ግን የመጠቀም ልምድ አለመኖር፡

4. **ማህበረሰቡ የሌለው ነገር ግን የመጠቀም መብት ያለዉ ሀብት**፡ ምሳሌ፡

- **ግብርና እና ተፈጥሮ ሀብትን በተመለከተ፡** ውሃን ለመስኖ ልማት የመጠቀም መብት ማህበረሰቡ ቢኖረውም በካባቢው ለመስኖ አገልግሎት የሚውል ውሃ አለመኖር፡ በሌላ አካባቢ ያሉ ገበያዎችን የመጠቀም መብት ቢኖርም ተደራሽነት አለመኖር፡

- **የማህበረሰብ ጤናን በተመለከተ**፡ ማህበረሰቡ በአካባቢው የጤና ነክ ስልጠናወችን የማግኘት መብት እያለው የጤና ማሰልጠኛ ተቋማት አለመኖር፡
- **ትምህርትን በተመለከተ፡** ማህበረሰቡ በአከባቢዉ ስልጠናዎችን የማግኘት (የመጠቀም) መብት እያለዉ የትምህርት ማሰልጠኛ ተቋማት ያለመኖር፡፡
- **ውሃ እና የአካባቢ ንጽህናን በተመለከተ፡** ንጹህ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት የማግኘት መብት እያለው አለማግኘት፡
- **መልካም አስተዳደርን በተመለከተ፡** ማህበረሰቡ ወቅታዊ መረጃ የማግኘት መብት እያለው ማግኘት አለመቻል፣ ብድርን የማግኘት መብት ቢኖርም የአበዳሪ ተቋማት ተደራሽ አለመሆን፡
- **መንገድን በተመለከተ**፡ ምርትን አምርቶ በተሻለ ዋጋ የመሸጥ መብት ቢኖርም ዘመናዊ የገበያ ማዕከል አለመኖር፣
- **ሴቶችና የስርዓተ ፆታ ጉዳይን በተመለከተ**፡ በሌላ አካባቢ ያሉ ገበያዎችን የመጠቀም መብት ቢኖርም ተደራሽነት አለመኖር፡
- **ወጣቶችን በተመለከተ**፡ ስልጠና የማግኘት መብት ቢኖርም የተለያዩ የስልጠና ተቋማት በአካባቢው አለመኖር፡
- **ህጻናትን በተመለከተ፡** በቀበሌው የጤና ተቋም፣ ት/ቤት፣ ወዘተ… ባይኖር በአጎራባች ቀበሌ የመጠቀም መብት መኖር፣

**እንቅፋቶች**

ዕንቅፋቶች ማለት ማህበረሰቡ በአከባቢው ያሉትን የልማት መልካም አጋጣሚዎችን አሟጦ እንዳይጠቀም ማነቆ የሚሆኑ ነገሮች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. **ማህበራዊ እንቅፋቶች**፡- ምሳሌ፡-

- ሴት ልጅ ተምራ የትም አትደርስም የሚል ኋላቀር አመለካከት፡
- ሴቶች ደካሞች ወይም ጥገኞች ናቸው የሚል ጊዜው ያለፈበት ልማዳዊ አስተሳሰብ፣
- ወጣቶች ለስራ ዝግጁ አይደሉም የሚል ልማዳዊ እምነት፣

2. **ኢኮኖሚያዊ እንቅፋቶች**፡- ምሳሌ፡-

- ትምርት ቤቶችን በአግባቡ ለማስተዳደር የሚያስችል በቂ የሆነ በጀት ያለመኖር፡፡
- የቴክኖሎጅና የመስሪያ ካፒታል እጥረት፣
- ኢኮኖሚያዊ ሀብቶች ለሴቶች ተደራሽ አለመሆን፣

3. **ፖለቲካዊ እንቅፋቶች**፡- ምሳሌ፣ አሉታዊ የሆነ የአመለካከት ልዩነት መኖር፡፡

4. **ቴክኒካዊ (ሙያዊ) እንቅፋቶች፡-** ምሳሌ፡- በሙያው የሰለጠነ የሰው ሃይል ወይም ቴክኖሎጂ በበቂ ሁኔታ ያለመኖር፡፡

***መንስኤዎች***

*እንቅፋቶችን በተመለከተ ውይይት ሲደረግ መንስኤዎቻቸው ነጥረው መውጣት ይገባቸዋል። ለምሳሌ፡- እንቅፋት የሆነው ጉዳይ ከትምህርት ገበታ ያለፈቃድ መቅረት ከሆነ ምክንያቱ ኋላቀር ባህላዊ ልማድ ሊሆን ይችላል። ሆኖም በዚህ ብቻ ማቆም አይገባም። ምን እይነት ኋላቀር ባህላዊ ልማድ እንደሆነ መገለጽ ይኖርበታል። ከላይ ከቀረበው ምሳሌ በመነሳት ኋላቀር ባህላዊ ልማዱ ያለዕድሜ ጋብቻ ሊሆን ይችላል። መልካም አጋጣሚዎችን፣ እንቅፋቶችንና መንስኤዎቻቸውን አብጥርጥሮ በግልጽ ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ፡ የትምህርት ተቋም መኖር መልካም አጋጣሚ ነው ብሎ መውሰድ በቂ አይደለም፡፡የመማሪያ ክፍል ብዛት፣ የመማሪያ መጽሃፍ፣ የመምህራን መጠለያ ብሎ በግልጽ ማሳየት ይገባል። በሌላ በኩል ደግሞ የማስተማር ስነ ዘዴን ባግባቡ አለመጠቀም፣የመማሪያ መጻህፍትና ሌሎች የትምህርት ቁሳቁሶች እጥረት፣ የመማሪያ ክፍል እጥረት፣የመምህራን መጠለያ በበቂ ሁኔታ አለመኖሩ መገለጽ አለበት።ለዚህም ምክንያቱ ህብረተሰቡ ስለ ትምህርት ያለው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ ሊሆን ይችላል።*

*ከዚህ በተጨማሪም መሬትን መልካም አጋጣሚ ነው ብሎ መውሰድ በቂ አይደለም፡፡ የመሬቱ ስፋት፣ ለምን አገልግሎት እንደሚውል በግልጽ ማሳየት ይገባል። በሌላ በኩል ደግሞ የአስተራረስ ዘዴው ደካማ መሆን ለአንድ ሰብል ምርት እንቅፋት መሆኑ መገለጽ አለበት። ለዚህም ምክንያቱ በቂ የኤክስቴንሽን አገልግሎት አለመኖር ሊሆን ይችላል።*

***የመፍትሄ ርምጃዎች***

*ይህም ማለት የልማት እንቅፋቶችን ለመቅረፍ የሚከናወኑ ድርጊቶች ወይም የሚወሰዱ ርምጃዎች ናቸው፡*

## ***የትግበራ ደረጃዎች***

- *መንስኤዎችን ለመቅረፍ/ለማስወገድ የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፡*

## መ. የተማአአዕ አቀራረብ ቁልፍ ጠቀሜታዎች

የተማአአዕ አስተቃቀድ ስነ-ዘዴ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

1. ጥቂት የሆኑ የአሳታፊ ዕቅድ መሳሪያዎችን ስለሚጠቀም ማህበረሰቡ በቀላሉ የአሳታፊ ዕቅድን ሂደት ማስተዳደር፣ (ማዘጋጀት፣ መተግበር፣ መከታተልና መገምገም) ይችላል፡፡
2. በዕለት ከዕለት የማህበረሰቡ የልማት ስራዎች ላይ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ያጎለብታል፡፡
3. የጥገኝነት አስተሳሰብን በመቅረፍ በራስ መተማመንን ያጠናክራል፡፡
4. ማህበረሰቡ በውሳኔው ላገኘው ውጤት ባለቤት እንዲሆን ያበረታታል፡፡
5. በየደረጃው ከማዕከል እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉትን የመንግስት አካላትን ለህዝቡ ተጠያቂ እንዲሆኑ፣ ወቅታዊ እና ተገቢ የሆነ ምላሽ እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡
6. ማህበረሰቡ ድህነቱን እንዲያስወግድ መሰረት የሚጥል ተመራጭ የሆነ የአስተቃቀድ ዘዴ ነው።
7. የታችኛው የመንግስት አካላት የልማት አጋሮችን ፕሮግራሞች የማስተባበር አቅማቸውን ያዳብራል፡፡

## ሠ. መንግስት የተማአአዕን መተግበር ለምን ፈለገ?

መንግስት ይህንን የአስተቃቀድ ስነ-ዘዴ ተቋማዊ ለማድረግ የወሰነበት ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

1. ይህ የዕቅድ ስነ-ዘዴ የሚጀምረው በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን የልማት መልካም አጋጣሚዎች በመለየት የልማት እንቅፋቶችን በራሱ እንዲያስወግድና ራስን የመቻል አስተሳሰብ ስር እንዲሰድ በማድረግ ነው፡፡ ይህ ከሌሎች አሳታፊ የአስተቃቀድ ስነ-ዘዴዎች ማለትም እንቅፋቶችን ቀድመው ከሚለዩና የጥገኝነት ስሜት ቀስ በቀስ ከሚያሳድሩት ልዩ ያደርገዋል።
2. ሌላው የዚህ አስተቃቀድ ስነ-ዘዴ መሰረታዊ ባህሪው የልማት ግቦችን በማሳካት የክልሉን መንግስት የልማት ራዕይ ዕውን እንዲሆን ስለሚያስችል ነው፡፡ የልማት ራዕዩም ህዝቡ የረጅም እና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችን በማዘጋጀት ራሱን ከድህነት ለማላቀቅ የሚያደርገውን ጥረት የሚያግዝ ነው፡፡ ሁሉም ቀበሌዎች ለልማት ጉዳዮቻቸው አንጻራዊ በሆነ መልኩ ተመሳሳይ የአስተቃቀድ ዘዴ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡
3. ይህ የአስተቃቀድ ስነ-ዘዴ የተዘጋጀው በታችኛው የመንግስት መዋቅር በተለይም በንዑስ ቀበሌ፣ በቀበሌ እና በወረዳ ደረጃ ለመተግበር በሚያስችል መልኩ ነው፡፡

4. ከዚህም በተጨማሪ የአስተቃቀድ ስነ-ዜዴው የተዘጋጀው የሀገሪቱ ህገ መንግስት ለህበረተሰቡ የሚሰጠውን መብቶች እንዲጠቀሙ እና ያልተማከለ አስተዳደር ሂደትን በማጠናከር የህብረተሰቡን የውሳኔ ሰጭነት ሚና ማጎልበት ነው፡፡

## ረ. ሌሎች የተማአአፅ ጠቃሚ መለያ ባህሪያት

የተማአአፅ የአስተቃቀድ ስነ-ዘዴ የሚከተሉትን ቁልፍ ባህርያት ያካትታል።

1. ይህ የአስተቃቀድ ዘዴ በዋነኝነት አሳታፊ መሳሪያዎችን ስለሚጠቀም ማህበረሰቡ በቀላሉ ሊቀበለው ይችላል፡፡
2. የተማአአፅ አስተቃቀድ ዘዴ ማህበረሰቡ በዕለት ከዕለት የሚያከናውናቸውን የልማት ተግባራት መሰረት ያደረገ ተጠያቂነት እና ግልጸኝነት እንዲጎለብት ያደርጋል፡፡
3. የአስተቃቀድ ስነ-ዘዴው ጥገኝነትን ለማስወገድ እና በራስ መተማመንን ለማጠናከር ዓይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡
4. ማህበረሰቡ በዚህ የአስተቃቀድ ዘይቤ በሰጠው ውሳኔ መሰረት በተገኙት አሉታዊ ይሁን አወንታዊ የልማት ውጤቶች ሙሉ ኃላፊነት እንዲቀበለ ያስችላል፡፡
5. በማህበረሰቡ ያለውን አስከፊ ድህነት ለማስወገድ መሰረት መጣል የሚያስችል እጅግ በጣም ተመራጭ የሆነ የአስተቃቀድ ዘይቤ ነው፡፡

## ሰ. የቀበሌውን ዓላማ፣ ግብ እና ዋና ዋና ተግባራት ከወረዳው የአጭር፣ የመካከለኛ ጋር ረጅም ጊዜ ዕቅድ ጋር ማስተሳሰር

# የትግበራ ደረጃዎች

**ደረጃ 1** **በየትኩረት ቡድኑ በቀበሌ ደረጃ መልካም አጋጣሚዎችን መወሰን፡፡**

**ተግባር 1፡** የትኩረት ቡድን አባላት መልካም አጋጣሚዎችን፣ እንቅፋቶች፣ መንስኤዎችንና መፍትሔዎች ለመለየት፡

1. በየትኩረት ቡድናቸው ሆነዉ እንዲቀመጡ ማድረግ
2. የትኩረት ቡድኑ አባላት በየቡድናቸው እንደተቀመጡ ከዚህ በታች የተገለጹትን ጥያቄዎችን እንዲመልሱ በመጠየቅ ያሉትን መልካም አጋጣሚ እንዲለዩ ማድረግ፡

እነዚህም፡

ሀ) ከየትኩረት ቡድኑ ስራዎች አኳያ ቀበሌው **ያለዉ** እና **በአግባቡ እየተጠቀመበት ያለ ሃብት** ምን ምን ናቸዉ? ተብሎ እንዲጠቅሱ መጠየቅ፣

**ለምሳሌ፡-**

- **ከግብርና አኳያ፡** የእንሰሳት ህክምና አገልግሎት /የእነሰሳት ጤና ኬላ/፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎት እና የብድር አገልግሎት ወዘተ በመኖሩ መጠቀም መቻላቸው፡
- **ከማህበረሰብ ጤና አኳያ፡** የክትባት አገልግሎት፣ የተመላላሽ በሽተኞች አገልግሎት፣ የጤና ሰራተኛ ወይም ባለሙያ፣ ለጤና ሰራተኞች የሚሆን መኖሪያ ቤት፣ በቂ የጤና መሳሪያዎችና ቁሳቁስ፣ ወዘተ
- **ከትምህርት አኳያ፡** ያሉ ሃብቶች (ምሳሌ፡ ዕድሜያቸዉ ለትምህርት የደረሱ ህጻናት፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ መምህራን፣ የመምህራን መኖሪያ ቤት፣ ጥሩ የስራ አፈጻጸም፣ ለንባብ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች፣ ወዘተ) ንኡስ
- **ከመንገድ አኳያ፡** መንገዶች፣ ህንጻዎች፣ ድልድዮች፣ መብራት ወዘተ፣
- **ከመልካም አስተዳደር አኳያ፡** የቢዝነስ እንቅስቃሴ እያስፋፉ ያሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የገንዘብና ብድር ቁጠባ ተቋማት፣ ድህነትን ለመዋጋት ቁርጠኝነት ያላቸው ወጣቶች መኖር፣ የዘላቂ ልማትና ድህነትን ማስወገድ ፕሮግራም መኖር፣
- **ከሴቶችና ስርዓተ ፆታ አኳያ እንዲሁም ከወጣቶችና ኤችአይቪ/ኤድስ አኳያ፡** ገቢ አመንጭ ቡድን መኖር፣ የንግድ ስራን የሚያበረታቱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መኖር፣ የገንዘብና ብድር ቁጠባ ተቋማት መኖር፣ በድህነት ቅነሳ ተግባር ላይ ራሳቸውን ያዘጋጁ ወጣቶች መኖር፣ የዘላቂ ልማትና ድህነትን ማስወገድ ፕሮግራም መኖር፣ የተፈጥሮ ሀብት መኖር፣

ለ) ከየትኩረት ቡድኑ ስራዎች አኳያ **ቀበሌው ያለው እና በአግባቡ ያልተጠቀመበት ሃብት** ምን ምን ናቸዉ? ተብሎ እንዲጠቅሱ መጠየቅ

**ለምሳሌ፡-**

- **ከግብርና እና ተፈጥሮ ሀብት አኳያ፡-** ለመስኖ ልማት የሚውል መሬት እንዲሁም የከርሰ ምድርና የገጸ ምድር ውሃ፣ በቢቢኤም በማንጣፈፍ ሊለማ የሚችል መሬት፣ ለንብ ማነብ ምቹ የሆነ አካባቢ፣ በግብርና ምርት ተግባር ላይ መሳተፍ የሚችልየወጣት ጉልበት በአካባቢው ቢኖርም በአግባቡ ጥቅም ላይ አለመዋል፣
- **ከማህበረሰብ ጤና አኳያ፡-** የክትባት አገልግሎት፣ የተመላላሽ በሽተኞች አገልግሎት፣ የጤና ሰራተኛ ወይም ባለሙያ፣ ለጤና ሰራተኞች የሚሆን መኖሪያ ቤት፣ በቂ የጤና መሳሪያዎችና ቁሳቁስ፣ ወዘተ መኖራቸውና በአግባቡ ጥቅም ላይ አለዋል፣

- **ከትምህርት አኳያ፡-** ዕድሜያቸዉ ለትምህርት የደረሱ ህጻናት፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ መምህራን፣ የመምህራን መኖሪያ ቤት፣ ጥሩ የስራ አፈጻጸም፣ ለንባብ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች፣ ወዘተ መኖርና በአግባቡ ጥቅም ላይ አለመዋል፡
- **ከመንገድአኳያ፡-** መንገዶች፣ ህንጻዎች፣ ድልድዮች፣ መብራት ወዘተ መኖርና ነገር ግን ቀበሌው በአግባቡ እየተጠቀመበት አለመሆኑ፣
- **ከመልካም አስተዳደር አኳያ፡** የቢዝነስ እንቅስቃሴ እያስፋፉ ያሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የገንዘብና ብድር ቁጠባ ተቋማት፣ ድህነትን ለመዋጋት ቁርጠኝነት ያላቸው ወጣቶች መኖር፣ የዘላቂ ልማትና ድህነትን ማስወገድ ፕሮግራም መኖር በአግባቡ ጥቅም ላይ አለመዋል፡
- **ከሴቶችና ስርዓተ ፆታ አኳያ እንዲሁም ከወጣቶችና ኤችአይቪ/ኤድስ አኳያ፡-** ገቢ አመንጭ ቡድን መኖር፣ የንግድ ስራን የሚያበረታቱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መኖር፣ የገንዘብና ብድር ቁጠባ ተቋማት መኖር፣ በድህነት ቅነሳ ተግባር ላይ ራሳቸውን ያዘጋጁ ወጣቶች መኖር፣ የዘላቂ ልማትና ድህነትን ማስወገድ ፕሮግራም መኖር፣ የተፈጥሮ ሀብት መኖር እና በአግባቡ ጥቅም ላይ አለመዋል፡

ሐ) ከየትኩረት ቡድኑ ስራዎች አኳያ **ቀበሌው ያለው እና በጭራሽ/ምንም ያልተጠቀመበት ሃብት** ምን ምን ናቸዉ? ተብሎ እንዲጠቅሱ መጠየቅ፡፡

- **ከግብርና ተፈጥሮ ሀብት አኳያ፡-** ለሩዝ ሰብል ልማት ተስማሚ የሆነ መሬት፣ ለደጋ ወይም ለቆላ ፍራፍሬ ልማት ሊውል የሚችል መሬት በአካባቢው ቢኖርም ጭራሽ ማምረት አለመቻል፣
- **ከማህበረሰብ ጤና አኳያ፡-** የክትባት አገልግሎት፣ የተመላላሽ በሽተኞች አገልግሎት፣ የጤና ሰራተኛ ወይም ባለሙያ፣ ለጤና ሰራተኞች የሚሆን መኖሪያ ቤት፣ በቂ የጤና መሳሪያዎችና ቁሳቁስ፣ ወዘተ ቢኖርም በጭራሽ ያልተጠቀመባቸው፣
- **ከትምህርት አኳያ፡-** ዕድሜያቸዉ ለትምህርት የደረሱ ህጻናት፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ መምህራን፣ የመምህራን መኖሪያ ቤት፣ ጥሩ የስራ አፈጻጸም፣ ለንባብ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች፣ ወዘተ ቢኖርም በጭራሽ ያልተጠቀመባቸው፣
- **ከመንገድ አኳያ፡-** መንገዶች፣ ህንጻዎች፣ ድልድዮች፣ መብራት ወዘተ ቢኖርም ጭራሽ ያልተጠቀመባቸው፣
- **ከመልካም አስተዳደር አኳያ፡** የቢዝነስ እንቅስቃ እያስፋፉ ያሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የገንዘብና ብድር ቁጠባ ተቋማት፣ ድህነትን ለመዋጋት ቁርጠኝነት ያላቸው ወጣቶች፣ የዘላቂ ልማትና ድህነትን ማስወገድ ፕሮግራም ቢኖርም በጭራሽ ያልተጠቀመባቸው፣

▪ **ከሴቶችና ስርዓተ ፆታ አኳያ እንዲሁም ከወጣቶችና ኤችአይቪ/ኤድስ አኳያ፡-** ገቢ አመንጭ ቡድን፣ የንግድ ስራን የሚያበረታቱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የገንዘብና ብድር ቁጠባ ተቋማት፣ በድህነት ቅነሳ ተግባር ላይ ራሳቸውን ያዘጋጁ ወጣቶች፣ የዘላቂ ልማትና ድህነትን ማስወገድ ፕሮግራም፣ የተፈጥሮ ሀብት ቢኖርም በጭራሽ ያልተጠቀመባቸው፣

መ) ከየትኩረት ቡድኑ ስራዎች አኳያ **ቀበሌው የሌለው ነገር ግን የመጠቀም መብት ያለው ሃብት** ምን ምን ናቸዉ? ተብሎ እንዲጠቅሱ መጠየቅ፡፡

▪ **ከግብርና አኳያ፡** ውሃን ለመስኖ ልማት የመጠቀም መብት ማህበረሰቡ ቢኖረውም በአካባቢው ለመስኖ አገልግሎት የሚውል ውሃ አለመኖር፣

▪ **ከማህበረሰብ ጤና አኳያ፡** የክትባት አገልግሎት፣ የተመላላሽ በሽተኞች አገልግሎት፣ የጤና ሰራተኛ ወይም ባለሙያ፣ ለጤና ሰራተኞች የሚሆን መኖሪያ ቤት፣ በቂ የጤና መሳሪያዎችና ቁሳቁስ፣ ወዘተ በቀበሌው ውስጥ ባይኖሩም/ከማህበረሰቡ ውጭ ከሆኑ/ ማህበረሰቡ የመጠቀም መብት ያለው፣

▪ **ከትምህርት አኳያ፡** የመማሪያ ክፍሎች፣ መምህራን፣ የመምህራን መኖሪያ ቤት፣ ጥሩ የስራ አፈጻጸም፣ ለንባብ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች፣ ወዘተ በቀበሌው ውስጥ ባይኖሩም/ከማህበረሰቡ ውጭ ከሆኑ/ ማህበረሰቡ የመጠቀም መብት ያለው፣

▪ **ከመንገድ አኳያ፡** መንገዶች፣ ህንጻዎች፣ ድልድዮች፣ መብራት ወዘተ በቀበሌው ውስጥ ባይኖሩም/ከማህበረሰቡ ውጭ ከሆኑ/ ማህበረሰቡ የመጠቀም መብት ያለው፣

▪ **ከመልካም አስተዳደር አኳያ፡** የቢዝነስ እንቅስቃሴ እያስፋፉ ያሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የገንዘብና ብድር ቁጠባ ተቋማት፣ ወዘተ በቀበሌው ውስጥ ባይኖሩም/ከማህበረሰቡ ውጭ ከሆኑ/ ማህበረሰቡ የመጠቀም መብት ያለው፣

▪ **ከሴቶችና ስርዓተ ፆታ አኳያ እንዲሁም ከወጣቶችና ኤችአይቪ/ኤድስ አኳያ፡** ገቢ አመንጭ ቡድን፣ የንግድ ስራን የሚያበረታቱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የገንዘብና ብድር ቁጠባ ተቋማት፣ ወዘተ በቀበሌው ውስጥ ባይኖሩም/ከማህበረሰቡ ውጭ ከሆኑ/ ማህበረሰቡ የመጠቀም መብት ያለው፣

**መልካም አጋጣሚዎችን ለመለየት በውይይት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውል ቼክሊስት/የውይይት ነጥቦች/ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡**

## ▪ ከግብርና እና ተፈጥሮ ሀብት አኳያ፡

✓ ግብዓቶች፣ በአካባቢው እና ከአካባቢው ውጭ የሚገኙ (ለሰብል እና ለእንስሳት ልማት የሚውሉ)

✓ የኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ (የሰብል ልማት፣ የተፈጥሮ ሀብትና የእንስሳት ባለሙያ)

✓ ለመስኖ ልማት አገልግሎት የሚውል የውሃ ሀብት (ወንዝ፣ ኩሬ፣ የዝናብ ውሃ)፣

✓ ገበያዎች (ወቅታዊ፣ ወርሃዊ፣ ሳምንታዊ)፣

✓ የፋይናንስ አገልግሎት (መደበኛና ኢ-መደበኛ)፣

✓ የቁጠባና ብድር ማህበራት፣

✓ የተባይ ቁጥጥር (ባህላዊና ዘመናዊ የተባይ ማጥፊያ መድኃኒቶች)፣

✓ የድኅረ ምርት ማከማቻ (በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ)፣

✓ የምግብ ማቀነባበሪያ ሁኔታዎች (በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ)፣

✓ የእርሻ ማሳ (በቤተሰብ ደረጃ)፣

✓ ለም መሬት (በቤተሰብና በቀበሌ ደረጃ)፣

✓ ዘመናዊ የእርሻ ዕውቀት (በራዲዮና በስልጠና/በውይይት)፣

✓ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ፕሮግራሞች

✓ የተፈጥሮ ሀብት በሰፊው መኖር/መገኘት፣

✓ የአካባቢ ጥበቃ ዘዴዎችና ልምዶች መኖር /ውሀና ተፋሰስን እንዲሁም የዱር እንስሳትን መንከባከብና መጠበቅ/፣

✓ የአፈር ክለትንና የሚቀንሱ እና የምርታማነት መታጣት ችግርን የሚቀርፉ ዘዴዎች መኖር ወዘተ ናቸው፡፡

- **ከማህበረሰብ ጤና አኳያ፡**

✓ የጤና ተቋማት፣

✓ የጤና አገ/ሽፋን ዕድገት፣

✓ የህጻናት ሞት፣

✓ ከአንድ ዓመት በታች  ያሉ ህጻናት ሞት መጣኔ፣

✓ ከአምስት ዓመት በታች ያሉ ህጻናት ሞት መጣኔ፣

✓ የእናቶች ሞት፣

✓ የወሊድ መቆጣጠሪያ አገልግሎት፣

✓ የቤተሰብ ዕቅድ፣

✓ በፕሮግራሞች መካከል የቅንጅት እጥረት፣

✓ ለፆታ ትኩረት አለመስጠት፣

- ✓ የጤና አገልግሎት መኖርና የጥገና አገልግሎት ሁኔታ መመቻቸት፣
- ✓ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር የመረጃ፣ ትምህርትና መገናኛ ቁሳቁሶች
- ✓ የኤች አይ /ኤድስ የምርመራና የህክምና አገልግሎት
- ✓ በፈቃድ ላይ የተመሰረተ የምክር አገልግሎት
- ✓ የቤት ለቤት እንክብካቤ መመሪያዎች ወዘተ ናቸው፡፡

- **ከትምህርት አኳያ፡**

- ✓ የትምህርት ተሳታፎ ምጣኔ መጨመር
- ✓ የመድገም ምጣኔን መቀነስ
- ✓ የትምህርት ጥራትን ማሻሻል
- ✓ በሴቶችና በወንዶች መካከል የሚታየውን የትምህርት ተሳትፎ ክፍተትን ማመጣጠን
- ✓ የማቋረጥን ምጣኔ መቀነስ
- ✓ የትምህርቱን ዘርፍ የበጀት ድርሻ ማሳደግ
- ✓ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚሰጠውን ትምህርት ውጤታማ ማድረግ
- ✓ የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ ግብር አተገባበር የተሻለ ደረጃ ማድረስ
- ✓ የስነ- ዜጋና ስነ- ምግባር ትምህርትን በማሻሻል መልካም ስነምግባር ያለዉን ዜጋ መፍጠር
- ✓ ተማሪ መምህር፣ ተማሪ መጽሃፍ እና ተማሪ ክፍል ጥምርታዎችን ማሳደግ
- ✓ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ተሳትፎን ማሳደግ
- ✓ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ምጣኔ ማሳደግ
- ✓ የትምህርት ተቋማት መኖርና የጥገና አገልግሎት ሁኔታ መመቻቸት፣

- **ከንጹህ መጠጥ ውሃና የአካባቢ ንጽህና አኳያ፡**

- ✓ እንዲያገግሙ የሚፈለጉ ነገር ግን የተጎዱ የአካባቢ የውኃ ሃብቶችን መለየት
- ✓ የዝናብ ውሃን ማሰባሰብ
- ✓ የመቀናጆ ሃብትን መለየት (ምን እገዛ እንደሚደረግ መለየት)
- ✓ የግል ባለሃብቱ የሚሣተፍበትን ሁኔታ መለየት
- ✓ የሃብት ብክለት መከላከል (የውሃን ብክለት ሊያመጡ የሚችሉ ሁኔታዎችን መለየት)
- ✓ የአካባቢና የግል ንጽህና አያያዝ አሁን ያለንበትን ሁኔታ መለየት
- ✓ በየቤቱና በየአካባቢው ለንጽህና አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውለውን ውሃ የማፋሰሻ ስርዓት ሁኔታ መለየት
- ✓ የውሃ አገልግሎትን ለማግኘት በሚሰሩ የግንባታ ስራዎች ላይ የህብረተሰቡ አመለካከት

- ✓ የመጠጥ ውኃ ዓመቱን በሙሉ ለማግኘት ያለ ሁኔታ
- ✓ የውሃ ተቋማት መኖርና የጥገና አገልግሎት ሁኔታ መመቻቸት ወዘተ ናቸው፡፡

## ▪ ከመልካም አስተዳደር አኳያ፡

◈ **የሞራልና የባህል መነሳሳት**

- ✓ የማህበረሰቡን ጥሩ ባህሎች ማስቀጠል
- ✓ ጠንካራ ሠራተኛ መሆንና ያለውን እውቀት የመጠቀም ችሎታ
- ✓ ለቤተሰብ እንክብካቤና ጥበቃ ማድርግ
- ✓ እርስ በርስ መከባበር
- ✓ እርዳታ የሚሹትን ማገዝ በተለይ አረጋዊያንን እና ህጻናትን ከችግር መጠበቅ

◈ **ህግና ደንብን የማክበር ጥንካሬ**

- ✓ ሰብዓዊ መብትን ማክበር
- ✓ የመኖርና ጥበቃ የማግኘት መብት
- ✓ የመናገርና የመጻፍ መብትና ነጻነት
- ✓ የመስራት መብት
- ✓ የመከበር መብት
- ✓ ማንኛውንም ሀይማኖት የመከተል መብት
- ✓ በህግ ፊት እኩል የመታየት መብት
- ✓ እኩል የዜግነት መብት
- ✓ እንደ ዜጋ የአገር ኃላፊነት
- ✓ በልማት ተግባራት የመሳተፍ መብት
- ✓ በሀገር ደህንነት ውስጥ የመሳተፍ መብት
- ✓ የተለያዩ የመንግስት ግብርን የመክፈል መብት
- ✓ በሀገሪቱ ህግ የመተዳደር መብት
- ✓ መሪ ለመሆን የህዝቡን ድምጽ በህግ፣ በደንቡና በመርህ የማግኘት መብት
- ✓ የቀበሌው ምክር ቤት አደረጃጀት  በመርህ የሚተዳደር መሆን
- ✓ የቀበሌው ምክር ቤት እና የልማት ኮሚቴው በስብሰባ ሀሳብን መለዋወጥ
- ✓ የሚሰጡ የተለያዩ መረጃዎች እውነትና ግልጽ መሆናቸው
- ✓ የህግ ማስፈጸሚያ መመሪያ መኖር

◈ **ሙስናና ሊሎች ከሞራል ውጭ የሆኑ ነገሮችን ማስዎገድ**

- ✓ የማህበረሰቡን የዕቅድ ግቦች መተግበርና መፈጸም
- ✓ የአካባቢ ጥበቃና ጽዳት
- ✓ ህግን በማንኛውም ጊዜ ማክበር
- ✓ በማህበራዊ አገልግሎት ክፍተት አለመኖር
- ✓ ውሃን በማባከን፣ ዛፎችን በመመንጠር፣ ከሰል በማክሰል፣ ቁጥቋጦዎችን በማቃጠል የአካባቢን ተፈጥሮ አለማራቆት፣

◈ **ድህነትን በመቀነስ ኑሮን ማሻሻል**

- ✓ የከፋ ድህነትን መቀነስ
- ✓ በምግብ እራስን የሚያስችል የእርሻ መሬት
- ✓ የተደራጁ አምራች ቡድኖች
- ✓ ብድር የማግኘት ሁኔታ
- ✓ የመሬት ተደራሽነትና ቁጥጥር
- ✓ ሙያዊ ስልጠና
- ✓ የግለሰብ የገቢ ምንጭ
- ✓ የእርሻ ስራ ገቢ ግብር፣ የተለያዩ ግብሮች
- ✓ ማህበረሰቡ ለስራ የሚያደርገው አስተዋጽኦ፣
- ✓ ከማህበረሰቡ ውጭ ያለ የገቢ ምንጭ
- ✓ የወፍጮዎች መኖርና የጥገና አገልግሎት ሁኔታ መመቻቸት፣
- ✓ የመንግስት ጽ/ቤቶች መኖርና የጥገና አገልግሎት ሁኔታ መመቻቸት፣

## ▪ ከመንገድ አኳያ፡

- ✓ የመንገዶች መኖር፣
- ✓ የመንገዶች የጥገና አገልግሎት ሁኔታ መመቻቸት፣
- ✓ የድልድዮች መኖር፣
- ✓ የድልድዮች የጥገና አገልግሎት ሁኔታ መመቻቸት፣

- **ከሴቶችና ስርዓተ ፆታ አኳያ፡**

✓ የሴቶችና የወንዶች ኃላፊነትና ሚና
✓ ለወንዶችና ለሴቶች የወሳኝ ሀብቶች ተደራሽነት
✓ ለገጠር ሴት ትኩረት የሰጡ ኢኮኖሚያዊ ፕሮጀክቶች
✓ ሴክተሮች የስርዓተ ፆታ ጉዳዮችን ለመተግበር የሚያስችሉ የፖሊሲ አቅጣጫዎች
✓ ለአብዛኛው ሴቶች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተደራሽነት
✓ ከመሀይምነት የተላቀቁ ወንዶችና ሴቶች ንጽጽር
✓ ሴቶች የራሳቸውን አካላትና ህይወት የመቆጣጠር ሁኔታ
✓ የጤናው ሴክተር  ስርዓተ-ፆታ ተኮር ስለመሆኑ
✓ ሴቶች በኤች አይ ቪ/ኤድስ ፕሮግራሞች ትኩረት ስለማግኘታቸው
✓ በሴቶችና ስርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች

- **ከወጣቶች አኳያ፡**

✓ የየቀኑን ፍላጎታቸውን ለማሟላት የቤተሰቦች የኢኮኖሚ አቅም
✓ ለምግብ፣ ለመጠለያና ለልብስ ያለው የኢኮኖሚ ተደራሽነት
✓ የኢኮኖሚ ቡድኖች ማቋቋም
✓ የብድሮች፣ የባንኮችና የቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት መኖር
✓ የአካባቢው የተፈጥሮ ሀብቶች በቀበሌው ውስጥ በብዛት መኖር
✓ በእያንዳንዱ ንዑስ ቀበሌ የወጣት ቡድኖችን  ማቋቋም
✓ ለሴቶችና ለወጣት ቡድኖች የብድር አገልግሎት ማቅረብ

- **ከህጻናት አኳያ፡**

✓ የህጻናት ፓርላማ በቀበሌና በትምህርት ቤት ስለመኖሩ
✓ የህጻናት ክበባት በት/ቤት ስለመኖሩ፣
✓ ለህጻናት ምቹ የመጫወቻ ቦታና ቁሳቁስ ስለመኖሩ
✓ በቤት ውስጥ ስላላቸው ተሳትፎ
✓ የህጻናት ደህንነትና ጥበቃ ጉዳይ ትኩረት ስለማግኘቱ፣
✓ ህጻናት ከአጉል ባህልና ልማድ እየተጠበቁ ስለመሆኑ፣
✓ በት/ቤት ውስጥ ስላላቸው ተሳትፎ ወዘተ…

**ደረጃ 2 በቀበሌ ደረጃ የተለዩትን መልካም አጋጣሚዎች በክብደታቸው ቅደም ተከተል ማስቀመጥ ፡፡**

**ተግባር 2፡** የትኩረት ቡድኑ አባላት ቀደም ብሎ የተዘረዘሩትን መልካም አጋጣሚዎችን እንደየ ክብደታቸው በቅደም ተከተል ማስቀመጥ።

1. የትኩረት ቡድኑ አባላት የቀበሌውን መልካም አጋጣሚ ከወሰዱ በኋላ ተመሳሳዮችን በማዋሃድ እንዲወስዱ እና 4 ወይም 5 መልካም አጋጣሚዎችን በጋራ እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡
2. መልካም አጋጣሚዎችን እንደየ ክብደት ደረጃቸው በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ የትኩረት ቡድን አባላትን መጠየቅ፡፡
3. ለደረጃ አሰጣጡም በጥንድ (pair-wise ranking) ወይንም በተሻይነት (preference ranking) ደረጃ አሰጣጥ ዘዴ መጠቀም ይቻላል፡፡
4. በደረጃዎች የተዘረዘሩትን በቀበሌው የተማአአፅ መዝገብ ላይ ማስፈር፡፡

**ደረጃ 3 ከየትኩረት ቡድኑ ስራ አኳያ መልካም አጋጣሚዎችን ለመጠቀም እንቅፋት የሆኑትን ጉዳዮች መለየት፣**

**ተግባር 3፡** በየትኩረት ቡድኑ ከተጠቀሱት መልካም አጋጣሚዎች አብዛኛዉን የቀበሌ ነዋሪዎችን እንዳይጠቀሙ ያደረጓቸውን ቢያንስ 3 እንቅፋቶች እንዲጠቅሱ ማድረግ፡፡ ይህም በሚከተሉት መንገድ የሚፈጸም ይሆናል፡-

1. እያንዳንዱን የትኩረት ቡድን ቅድሚያ ሊሰጣቸዉ የሚገባቸዉን 2 ዋነኛ መልካም አጋጣሚዎችን ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ያገዱ ቢያንስ 3 እንቅፋቶችን እንዲጠቅሱ መጠየቅ፣
2. እንቅፋቶቹም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ መዋቅራዊ፣ ባህላዊ፣ ቴክኒካዊ እና ከባህሪ ጋር የተያያዙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
3. የተዘረዘሩትን እንቅፋቶች በዕቅድ መመዝገቢያ ሰንጠረዡ [ዓምድ # 3] መመዝገብ፣

**ደረጃ 4 መልካም አጋጣሚዎችን ከመጠቀም ያገዱ እንቅፋቶች <u>መንስኤዎችን</u> መወሰን፡፡**

**ተግባር 4፡** መልካም አጋጣሚዎችን ከመጠቀም ያገዱ የእንቅፋቶች መንስዔዎችን እንዲጠቅሱ የትኩረት ቡድኑን አባላት መጠየቅ፡፡

1. እያንዳንዱ የትኩረት ቡድን ቅድሚያ ሊሰጣቸዉ የሚገባቸዉን 2 ዋነኛ መልካም አጋጣሚዎችን ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ያገዱ ቢያንስ 3 የእንቅፋቶች መንስኤ እንዲጠቅሱ መጠየቅ፣

2. መንስኤዎችም ሲዘረዘሩ አንገብጋቢ (immediate)፣ ትኩረት የሚሻ (underlying) እና መሰረታዊ (Basic) መንስኤዎች በሚሉት መልኩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

3. መንስኤዎቹም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ መዋቅራዊ፣ ባህላዊ፣ ቴክኒካዊ እና ከባህሪ ጋር የተያያዙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

4. ቅድሚያ ተሰጥቷቸዉ የተዘረዘሩትን መንስኤዎች በዕቅድ መመዝገቢያ ሰንጠረዥ [ዓምድ#4] መመዝገብ፣

**ደረጃ 5 በቀበሌ ደረጃ የየትኩረት ቡድኑን ስራ የሚገልጽ ቴክኒካዊ መረጃ መሰብሰብ፡፡**

**ተግባር 5፡** የእየትኩረት ቡድኑ አባላት የቴክኒክ መረጃዎች አሰባሰብ ላይ እገዛ ያደርጋሉ፡፡

1. መረጃውን ለመሰብሰብ እንዲያግዟቸው የአርሶ አደር፣ የወጣቶች፣ የሴቶች፣ እንዲሁም የሌሎች ተቋማት አመራሮች እነማን እንደሆኑ የትኩረት ቡድን አባላትን መጠየቅ፡፡

2. ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ የሚሰበሰቡ ቴክኒካል መረጃዎች እንዴት እንደሚሰበሰቡ ቅፆቹ **ከገጽ 64 እስከ 84** እንዳሉ ማሳየት፡፡

3. የተዘረዘሩትን ቴክኒካዊ መረጃዎች በቀበሌው የተማአአዕ መዝገብ ላይ ማስፈር፡፡

## በ2ኛው ቀን

**ደረጃ 6 እያንዳንዱ የትኩረት ቡድን የሚመለከተውን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ወይም የአገግ መሳሪያዎችን /PRA Tools/ በመጠቀም መረጃ ማሰባሰብ፣**

**ተግባር 6፡ የትኩረት ቡድኖች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የአገግ መሳሪያዎች /PRA Tools/ በማዘጋጀት ተጨማሪ መረጃዎችን ይሰበስባሉ፣**

- ## ከግብርና እና ተፈጥሮ ሀብት አኳያ፡

1. ወቅታዊ የጊዜ መቁጠሪያን ትርጉምና ጠቀሜታ መግለጽ፣

2. ለአብነት ያህል፣ ወቅታዊ የጊዜ መቁጠሪያ ብዛት ያላቸውን የተለያዩ መረጃዎች በጋራ የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ የሚያሳይ ሲሆን የማህበረሰቡን የሥራ እንቅስቃሴዎች ወር በወር፣ በዘርፍ

ወሰን ውስጥ በመሆን ያነፃፅራል። ዘወትር (normal year) ዑደታቸውን ጠብቀው በየዓመቱ የሚከሰቱ ተግባራትን ይለያል።

3. ወቅታዊ የጊዜ መቁጠሪያ ሲዘጋጅ በማህበረሰቡ ዘንድ በመደበኛነት ወይም ዘወትር ይከሰታል ተብሎ የሚታመንበት ዓመት መሆን ይገባዋል።

4. የትኩረት ቡድኑ በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ መረጃዎችን ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል፣

- የአየር ንብረት እና የዝናብ መጠን /የዝናብና የውሃ መኖርን/፣
- የምግብ መገኘት /መቼ ከበቂ በላይ ምግብ እንደሚኖር እና መቼ እጥረት እንደሚከሰት/፣
- የእንስሳት ጤንነት ሁኔታ /ምን ዓይነት በሽታዎች ከብቶችን፣ በጎችንና ፍየሎችን እንደሚያጠቁ/፣
- የሰብል ልማት እንቅስቃሴዎች /የጤፍ፣ ስንዴ ወዘተ የእርሻ ሥራዎች እንቅስቃሴ/
- የጉልበት አጠቃቀም /የትኞቹ ወራት ናቸው ለሴቶች እና ለወንዶች በጣም ጉልበት የሚጠይቁት/፣

5. መቼ ጤፍ ትዘራላችሁ? መቼ ትሰበስባላችሁ? እና የመሳሰሉ ጥያቄዎች የቡድን ውይይቶች አካል ሆነው ይቀርባሉ፣

6. ወቅታዊ የጊዜ መቁጠሪያው ተዘጋጅቶ ሲያልቅ መረጃው ትክክል ስለመሆኑ እያንዳንዱን አባል መጠየቅና ማረጋገጥ፣

7. የተዘጋጀው ወቅታዊ የጊዜ መቁጠሪያ በቀበሌው የተማአአፅ መመዝገቢያ መዝገብ ላይ መመዝገብ፣

## ▪ ከማህበረሰብ ጤና አኳያ፡

1. ለጤና አገልግሎት አፈጻጸም የአዝማሚያ ማሳያ መስመር ትርጉምና ጥቅም መግለጽ፣

2. የጤና አገልግሎት አፈጻጸም የአዝማሚያ ማሳያ መስመር ምን ማለት እንደሆነ ለትኩረት ቡድኑ ማስረዳት፣

3. የጤና አገልግሎት አፈጻጸም የአዝማሚያ ማሳያ መስመር በመስራት ልምምድ ለማድረግ ቀላል የሆነው ግራፍ በመጠቀም መግለጽና በኤክስ /አግድም መስመር / እና ዋይ መስመር /ቋሚ መስመር/ ላይ እንዴት ዓመቶች ወይም ዓመት ምህረቶች ተለዋዋጭ ልኬታ /variable የመቀነስና የመጨመር ጋር እንደሚዛመድ መግለጽ / ለምሳሌ፣ ባልተመጣጠነ ምግብ የሚሞቱ፣ በወባ የተጠቁ በሽተኞች ቁጥር፣ የምግብ ዋስትና ሁኔታ ወዘተ/ ፣

4. በጽንሰ ሐሳቡ ላይ የትኩረት ቡድኑ ግንዛቤው አድጓል ተብሎ ሲታሰብ የኤክስ እና የዋይ አክሲስ መስመሮችን እንዲስሉ በማድረግና በኤክስ መስመር ላይ በእኩል እርቀት በመከፋፈል ዓመተ ምህረቶችን በሌላ በኩል ተለዋዋጭ ልኬታ በዋይ መስመር እንዲአሳዩ ማድረግ ፣
5. የትኩረት ቡድኑ አባላት ከምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡ የበሽታ ዓይነቶችን ለመቁጠር እንዲችሉ ጠጠር፣ አበባና ሌሎች ቁሳቁሶችን መጠቀም፣
6. የጤና አገልግሎት አፈጻጸም የአዝማሚያ ማሳያ መስመር ከተሳለና ስለትክክለኛነቱ በትኩረት ቡድኑ አባላት ከተረጋገጠ በኃላ ከቡድኑ አባላት አንዱ ቻርቱን ወይም ግራፉን በቡድኑ አባላት ፊት በሌላ ካኪ ወረቀት ላይ እንዲስለው ማድረግ፣
7. የሚታዩ ለውጦች የመጡበትን ምክንያቶች ከትኩረት ቡድኑ ጋር በመወያየት መለየት፣ ይህም ዋና ችግሮች፣ መልካም ተሞክሮዎችን ወይም ችግሮችን ለመፍታት የሚያገለግሉ ተግባራትን ለማወቅ ያግዛል፡
8. የጤና አገልግሎት አፈጻጸም አዝማሚያን ለማየት የሚረዱ፡-
- ከምግብ ጋር በተያያዘ የሚመጡ በሽታዎች /ምሳሌ፡- ያልተመጣጠነ ምግብ፣ እከክ፣ የከፋ ርሃብ፣ የአጥንት መሰልሰል ወይም መቅጠን/፣
- ከዝናብ ጋር የተያያዘ በሽታ /ምሳሌ፡- ወባ፣ ተቅማጥ፣ የሳንባ በሽታ/፣
- የምግብ ዋስትናና ተደራሽነት /ምግብ በብዛት መኖር እና የምግብ እጥረት/፣
- የሞት ምጣኔ /ምሳሌ፡ የተመጣጠነ ምግብ አለመኖርና በወባ ምክንያት የሚከሰት/፣

9. የጤና አገልግሎት አፈጻጸም የአዝማሚያ ማሳያ መስመር የሚያሳይ ቻርት ስለው ከጨረሱ በኃላ ሥራው ትክክል ስለመሆኑ ማንኛውንም የትኩረት ቡድን አባል መጠየቅ ይቻላል ፡፡
10. የጤና አገልግሎት አፈጻጸም አዝማሚያን በዕቅድ ሰንጠረዥ መመዝገብ።

## ▪ ከትምህርት አኳያ፡

1. የማህረሰቡ ካርታ ንድፍ ትርጉምና አስፈላጊነት መግለፅ፡፡
2. ቡድኑን የማህበረሰቡ የካርታ ንድፍ በመሬት ላይ እንዲያሳዩ ማድረግ፡፡
3. የካርታውን ንድፍ ስራ በአከባቢዉ በሚገኙ ነገሮች ለምሳሌ፡ ድንጋይ፣ እንጨት፣ ከሰል፣ ሳር፣ አመድ ወዘተ መጠቀም ይቻላል፡፡
4. የተዘጋጀዉ የቀበሌዉ የካርታ ንድፍ አቅጣጫ ያለዉ ሆኖ የመሬቱን አጠቃላይ አቀማመጥ ሁኔታ እና ያሉትን ሃብቶች በሚገልጽ መልኩ መሆን ይገባዋል፡፡ይህም ሲባል የንኡስ ቀበሌ

የመለያ ወሰን፣ ተቋማት፣ ተራሮች፣ ወንዞች፣ መሰረተ ልማት እና የአጎራባች ከተማ የመለያ ወሰን፡ የመሳሰሉት ተለይተው በካርታው መስፈር ይገባቸዋል፡፡

5. የትኩረት ቡድኑ በተዘጋጀዉ የካርታ ንድፍ ትክክለኛነቱንና ገላጭነቱን ከተስማሙበት በኋላ ወደ ወረቀት ላይ መሳል (መገልበጥ)፡፡

6. የትኩረት ቡድኑ አባላት ለካርታ ንድፍ ስራ ላበረከቱት የተሳካ አስተዋጽኦ የተማአአዕ አመቻቾች ማመስገን ይኖርባቸዋል፡፡

7. በተዘጋጀዉ ካርታ ላይ መታየት ከሚጠበቅባቸዉ ነገሮች(ዓይነቶች) ዉስጥ፡-

- የቀበሌ እና የንዑስ ቀበሌ ወሰን፣
- የዉሃ ጣቢያ፣ ግንባታ እና የዉሃ ማጠራቀሚያ ታንከር ያሉበት፣
- ቤቶች (በተለይም ማህበረሰቡ የሚኖርባቸዉ ግንባታዎች)
- የእርሻ ማሳዎች፣ የግጦሽ መሬት፣ ሜዳ፣ ጫካዎች
- የመሰረተ ልማት ዝርጋታ
- የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ግንባታዎች
- ተራራዎች ወይም ኮሮብታዎች
- አስፈላጊ የሆኑ በመሬት ላይ የሚታዩ መልካምድራዊ ገጽታዎች ወዘተ፡፡

8. የቀበሌው የካርታ ንድፍ በወረቀት ላይ ተገልብጦ በሚጠናቀቅበት ወቅት መረጃዎቹ ገላጭ ስለመሆናቸዉ እያንዳንዱን አባል መጠየቅ ይገባል፡፡

9. የቀበሌዉንም የካርታ ንድፍ በቀበሌዉ የተማአአዕ መዝገብ ላይ ማስፈር

## ▪ ከንጹህ መጠጥ ውሃና የአካባቢ ንጽህና አኳያ፡

1. በመጀመሪያ የአካባቢ የቅኝት ጉዞን ትርጉምና አስፈላጊነት በግልጽ ማስረዳት

2. ለምሳሌ በየሰፈሩ በሚደረገው እይታ ወቅት የየንዑስ ቀበሌው ድንበር ካርታ እና በውስጡ ስለሚገኙ ሃብቶች ተለይቶ ሊመዘገብ ይችላል።ተግባሩንም በየቀበሌው የሚገኙ የስራ አንቀሳቃሾች ማለትም የግብርና ባለሙያዎች ወይም የቀበሌው ስራ አስኪያጅ ወይም ከውሃ ኮሚቴ አባላት ሊሆን ይችላል።

3. በጉዞው (በቅኝቱ) ወቅት አመቻቾች፣ የቀበሌው ስራ አስኪያጅና የትኩረት ቡድኑ አባላት በቅኝቱ የሚታዩትን ሁኔታ ይመዘግባሉ፣ የቅኝቱን አላማ፣ የእይታውን ሂደት ለምሳሌ የአካባቢው ተፈጥሮ ሃብት መራቆት ሊሆን ይችላል ሁኔታውም ከሌሎች ሁኔታዎች ጋር ያለውን ዝምድና ይደሰሳል፡፡ ለምሳሌ ጥብቅ የሚሆኑ ቦታዎች፣ ለምግብ ሰብልና ለቋሚ ተክሎች የሚሆኑ ቦታዎች ሌሎችንም ሁኔታዎች ለመለየት ያስችላል።

4. በቅኝቱ ወቅት የታዩትና የተሰበሰቡት መረጃዎች የቀበሌውን ንድፍ ካርታ ስናዘጋጅ ለማረጋገጫነትም እንጠቀምባቸዋለን

5. እነዚህ መረጃዎች በሙሉ ለቀበሌው የተማአአዕ ስራዎች መሰረት ሆነው ያገለግላሉ

6. ከቅኝቱ ስራ በኋላ የቅኝቱ ቻርት ወዲያውኑ ወደ መዝገብ እንዲሰፍር ይደረጋል

7. የስራ ቡድኑ በቅኝቱ ወቅት የታዩትን ሁኔታዎች በየፈርጁ በሚከተለው ሁኔታ ያስቀምጣሉ፡፡

- **የአፈሩ ዓይነቶች፡-** ጥቁር ዓፈር፣ቀይ ዓፈር፣ለም አፈር፣ አሸዋማ፣ ሸክላማ አፈር በማለት ያሰፍራሉ
- **የዕጽዋት ዓይነቶች፡-** ግራር፣ የተፈጥሮ ዛፎች፣ የተተከሉ ዛፎች፣ ሳሮች፣ የስንዴ ማሳ ፣የጤፍ ማሳ፣ የግጦሽ መሬት፣ የፍራፍሬ ተክሎች ወዘተ… ተብለው ይመዘገባሉ
- **የዕርሻ ስራ ዓይነቶች፡-** የአበባ ተክሎች፣ ድብልቅ የዕርሻ ዓይነቶች፣ ለገበያ የሚመረቱ ሰብሎች፣ የከብቶች ዕርባታ፣ የጓሮ አታክልት ምርት ሁኔታ… ወዘተ በዝርዝር ይመዘገባሉ
- **የህዝቡ አኗኗር ወይም የአሰፋፈር ሁኔታ፡-** የመኖሪያ ሰፈሮች፣ የጋራ መጠቀሚያ ግንባታዎች፣ ጽ/ቤቶች፣ ት/ቤቶች፣ ጤና ኬላዎች፣ የከብት ህክምና ተቋሞች ወዘተ… ይመዘገባሉ
- **የአገልግሎት ሰጪ ተቋሞች ዓይነት፡-** ሱቆች፣ ጽ/ቤቶች፣ ት/ቤቶች፣ ውኃዎች፣ መብራት፣ መንገድ፣ ድልድዮች፣ ወፍጮ ቤቶች፣ የውኃ ጉድጓዶች፣ ግድቦች፣ ወንዞች፣ የህብረት ስራ ማህበራቶች ወዘተ በዝርዝር ይመዘገባሉ
- **ምቹ ሁኔታዎች፡-** ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ የዕርሻ አመራረት ሁኔታ፣ የዕውቀት ደረጃ ለምሳሌ የሰለጠነ፣ በከፊል የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ የሚታረስ መሬት፣ የከብት ርባታ ሁኔታ፣ የመሸጥና የመግዛት ሁኔታ፣ የማጓጓዣ ሁኔታ ወዘተ በዝርዝር ይሰፍራሉ
- **አደናቃፊ ሁኔታዎች ወይም ችግሮች፡-** በቂ መሬት አለመኖር፣ የተጨናነቀ አሰፋፈር፣ የንጽህና ችግር፣ የአፈር መከላት፣ የበሽታዎች ወረርሽኝ፣ ኋላ ቀር አስተሳሰቦችና ድርጊቶች፣ የጤና ችግር፣ የትምህርት ሁኔታ፣ በቂ ምርት አለመኖር፣ ተገቢ የሆነ የማዳበሪያ አጠቃቀም አለመኖር፣ ወዘተ ይዘረዘራሉ

8. የቅኝት ምዝገባው እንዳለቀ ሁሉም የስራ ቡድን አባላት በተሰራው ስራ የተስማሙ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል

9. የቅኝቱን ዝርዝር ወደ ቀበሌው የተማአአዕ መዝገብ እንዲሰፍር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## ▪ ከመልካም አስተዳደር አኳያ፡

1. የተቋማት ትንታኔ ትርጉምና ጠቀሜታን መግለጽ

2. የተቋማት ትንታኔ የሚጠቅመው በማህበረሰቡ ውስጥ ስለ አሉት  የተለያዩ  ቡድኖች ለማዎቅ ነው።

3. ዘዴው የሚረዳው የማህበረሰቡ አባላት በተለያዩ ተቋማት ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ፣ በተለይ ተቋሙቹ ለማህበረሰቡ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ ለመገንዘብ እና ተቋሙቹ ለማህበረሰቡ ጠቀሚታቸው  እንዴት እንደሚታይ ለመለየት ነው፡፡

4. አስተባባሪው ተሳታፊዎች ካርዶችን በተለያየ መጠን እንዲቆርጡ በማድርግ በተለያየ መጠን ባለው ካርድ ላይ የተቋማቱን ስም ይስጡ።

5.  ብዙ ጠቀሜታ ያለው ተቋም  ትልቅ ካርድ ማመልከት ይኖርበታል።

6. ተቋማቱ  ከማህበረሰቡ ልማት ጋር ያላችውን  ግንኙነት በመግለጽ ይዘርዝሩ፡፡ ከኗሪዎቹም መካከል የተጠቀሱት ተቋማት የሚሰሩትን ስራ ባጭሩ እንዲገልጹ ይጋብዟቸው

7. ለማህበረሰቡ ሰለ ተቋሙቹ ሚና፣ ተግባራትና ስለ ሀብት መሰረታቸው እንዲገልጹ ጊዜ ይስጧቸው

8. የትኩረት ቡድኑን በጋራ በሚሰጥ ደረጃ ወይም ነጥብ /collectively rank/ ተቋሞቹና ሃብቶቻቸው ለማህበረሰቡ እድገት ያደረጉትን አስተዋጽኦ መሰረት በማደረግ ደረጃ እንዲሰጡ ይጠይቁ። ውይይቱ በጥያቄ ሊጀምር ይችላል፡፡ "የትኛው ተቋም ውይም ሃብት የበለጠ የማህበረስቡን ልማት አሻሽሏል?"

9. ስለ ተቋሙቹና ሃብቶቻቸው በጥንድ በሚሰጥ ደረጃ ውይም ነጥብ /pair-wise ranking/ ዘዴ በመጠቀም ደረጃ መስጠት ይቻላል።

10. የትኩረት ቡድኑ አባላት ልማት ማለት ለነሱ ምን ማለት እንደሆነ እንዲወስኑ ያድርጉ፣ የብድኑን አባላት ዘርዘር ያለ መስፈርት እንዲያወጡ ይጠይቁ።

11. ቀጣዩ ደረጃ ተቋማቱን እና ሃብቶቻቸውን በቬንዳያግራም /Venn diagram/ መሳል ይሆናል

12. ወረቀቶችን በክብ መልክ በሦስት ወይም በአራት አይነት ስፋት ይቁረጡ

13. ለተሳታፊዎቹ ወረቀቶቹን መሬት ላይ በማስቀመጥ የስፋት መጠናቸው ምን ማለት እንደሆነ ይግለጹላቸው፡፡ (የወረቀቱ ስፋት የሚያሳየው  ተቋማቶቹና እና ሀብቶቻቸው ለማህረሰቡ በሰጡት ጠቀሚታ መጠን ነው።) ወረቀቶቹን በማንሳት የሚወክሉትን ተቋም እና ሃብት ከሚሰጡት ጠቀሜታ ጋር መመጣጠኑ  ስምምነት ላይ ይደረስ፡፡

14. ከክብ ወረቀቶቹ በኋላ በትልቅ ወረቀት /flipchart/ ክቦቹ ማነን እንደሚዎክሉ ለማህበረሰቡ ያስተዋውቁና ገለጻ ይድርጉ፡፡ የክብ ወረቀቶቹና በትልቁ ወረቀት ያሉት ክቦች ማህበረሰቡ ከተቋሙቹ እንዴት ተጠቀሚ እንደሆነ ያሳያል።. ምናልባት አብዛኛው ማህበረሰብ ከተቋሙቹ ተጠቀሚ ከሆነ በክብ መልክ የተቀረጸው ወረቀት በትልቁ ወረቀት ከተሳለው ክብ ውስጥ ወይም

ጥግ ማድርግ ተጠቃሚ ካልሆነ ተቃራኒውን ማስቀመጥ። ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ ተቋማትን የሚወክሉ ክቦችን በትልቁ ወረቅት ላይ ማስቀመጥ፡፡

15. ስምምነት በተደረሰበት መሰረት ሁሉንም ተቋማት በሚዎክሎቸው ክቦች በትልቁ ወረቀት ላይ መሳል እና ትልቁን ወረቀት ቦታ ስጥቶ ማስቀመጥ፣

16. የሚቀጥለው ደረጃ እነዚህ ተቋማት በማህበረሰቡ ውስጥ እርስ በርሳቸው እንዴት ግንኙነት እንዳላቸው ማሳየት፣

17. ተሳታፊዎችን ተቋማቶቹ እንዴት ለማህበረሰቡ ይጠቅሙ እንደ ነበር የተሰራበትን የቅርቡን ትልቅ ወረቀት /flipchart/ በማስታዎስ፣ በሌሎች ተቋማት ላይ ተመሳሳይ ልምምድ እንዲያደርጉና ተቋሞቹ የሚተባበሩ ውይስ የማይተባበሩ መሆናቸውን ማሳየት። ክብ ወረቀቱን በመጠቀም በሁሉም በቀበሌው በሚገኙ ተቋማት ግንኙነትና ጠቀሚታ ላይ በስፋት መወያየት

18. እንደጨረሱ መረጃዎቹ ትክክልኛ ስለመሆናቸው ሁሉንም ይጠይቁ።

19. መረጃውን በቀበሌው የተማአአዕ ዕቅድ መዝገቢያ ደብተር ላይ ይመዝግቡ።

- **ከመንገድ አኳያ፡**

1. ታሪካዊ የጊዜ ማሳያ መስመርን ትርጉምና ጠቀሚታ መግለጽ፡፡

2. ለምሳሌ "ቀበሌው የተመሠረተው ከሰዎች ፍልሰት ወይም ስደት ጋር በተያያዘ ነው" ብሎ መግለፅ ይቻላል።

3. ታሪካዊ የጊዜ ማሳያ መስመር ህብረተሰቡ ያለፈባቸውን ኩነቶች በትክክል የሚገልጽበት መሳሪያ መሆኑን የትኩረት ቡድኑ አባላት እንዲረዱ ማድረግ ያስችላል። በተጨማሪም ባለፉት ጊዜያት መልካም አጋጣሚዎችንና ከባድ ሁኔታዎችን ከልማት እንቅስቃሴ ጋር እንዴት እንዳዛመዷቸው ለማወቅ ዕድል ይፈጥራል።

4. ውይይቱ በዝግታ ሊጀመር ይችላል።ይህ ከሆነ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ስብሰባውን መክፈት ይቻላል።

- በቀበሌው ለመጀመሪያ ጊዜ መስፈር መቸ ተጀመረ?
- የአካባቢው መስራቾች እነማን ነበሩ?
- የሚያስታውሷቸው በመጀመሪያ የተከሰቱ ጠቃሚ ኩነቶች የትኞቹ ናቸው?
- ከሌላ አካባቢ ወደ ቀበሌው ወይም ከቀበሌው ወደ ሌላ አካባቢ የተካሄደ ስደት ነበርን?
- ከባድ የድርቅ አደጋ፣ የበሽታ ወረርሽኝ፣ ረሀብ፣ የጎርፍ መጥለቅለቅ፣ ወይም ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ተከስተው ነበርን?

- የአካባቢያችሁ ህብረተሰብ ከሠራቸው ሥራዎች ውስጥ የተወሰኑት ምን ምን ናቸው ብሎ መጠየቅ?
- በጣም ደስ ከሚያሰኙ ጊዜዎች መካከል የተወሰኑት የትኞቹ ናቸው?

5. የ2ኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭን በመጠቀም የሚለዩ ኩነቶችም እንደመነሻ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡
6. ለታሪካዊ የጊዜ ማሳያ መስመር ጠቃሚ ናቸው ተብለው ከሚጠቀሱ ነገሮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- የአየር ንብረትና የዝናብ ለውጥ (የዝናብና የውሃ መብዛትና እጥረት መኖር)
- በሰዎች ጤና ላይ የሚደርሱ ችግሮች (የበሽታ መስፋፋት ወይም ወረርሽኝ)
- የምግብ አቅርቦት ሁኔታ (ከበቂ በላይ መኖር ወይም እጥረት መኖር)
- የእንስሳት ጤና ሁኔታ (የላሞችና ፍየሎች ወዘተ ወረርሽኝ በሽታ )
- የሰብል ምርት (በጤፍ  እና ስንዴ ምርት ውጤት ወዘተ የተገኘ ስኬት)
- የጉልበት ሁኔታ (የጉልበት ሠራተኛ በከፍተኛ ደረጃ መጨመር ወይም መቀነስ)
- የፖለቲካ ሁኔታ መሻሻል (ሴቶችና ወጣቶችን  በአመራር ቦታ በማስቀመጥ ረገድ የተገኘ ስኬት)
- የማህበራዊ ሁኔታ መሻሻል (ከፍተኛ ግጭት የነበረበት ወቅት፣ ወዘተ)
- በመሠረተ ልማት ዝርጋታ የታየ ለውጥ (መንገድ፣ የውሃ ቧንቧ፣ትምህርት ቤት፣ የጤና አገልግሎት ወይም ሌሎች ትልልቅ ግንባታዎች ወዘተ የተገነቡበት ጊዜ)

7. ከላይ የተጠቀሱትን ኩነቶች ምክንያት በማድረግ የተገኙ ጥቅሞች ወይም ጉዳቶች ምን እንደሆኑ የትኩረት ቡድኖች መወያየት ይኖርባቸዋል፣
8. የደረሱ ጉዳቶችን ለመቀነስ የተደረጉ ጥረቶች ምን እንደነበሩ የትኩረት ቡድኖችን መጠየቅ ያስፈልጋል
9. ጉዳቶች የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ ለመቀነስ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎቸ የነበሩ ስለመሆናቸውም የትኩረት ቡድን አባላትን መጠየቅ
10. ታሪካዊ የጊዜ ማሳያ መስመር የማዘጋጀት ተግባር ከተጠናቀቀ በኋላ በትክክል ስለመሰራቱ እያንዳንዱን የትኩረት ቡድን አባል በመጠየቅ የተዘጋጀውን ታሪካዊ የጊዜ ማሳያ መስመር በቀበሌው የተማአአዕ መዝገብ ላይ ማስፈር

## የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ ለማህበረሰብ ለውጥ

ማህበረ ብርሃን ቀበሌ በአማራ ክልል፣ ምስራቅ ጎጃም ዞን በእነማይ ወረዳ የምትገኝ ስትሆን የቀበሌዉ ህዝብ ብዛት 8,223 ሲሆን ከነዚህም ዉስጥ 4,165 ሴቶች ናቸዉ፡፡ ቀበሌዋ

ከወረዳዉ ዋና ከተማ በ 8 ኪሎ ሜትር ርቀት በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ትገኛለች፡፡ ጎኛ በማህበረ ብርሃን ቀበሌ ዉስጥ ከሚገኙ ጎጦች አንዷ ስትሆን ከዋናዉ የአስፋልት መንገድ በ 4 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ በቀበሌዉ 500 አባወራዎች እና እማወራዎች የሚኖሩ ሲሆን ከፍተኛ የሆነ የጤፍ ምርት ከሚመረትባቸዉ ጎጦች ዉስጥ አንዷ ነች፡፡ የአካባቢዉ አፈር ጥቁር እና በክረምት ወቅት ለጎርፍ ተጋላጭ በመሆኑ እና ዉሃ በመቋጠር ከፍተኛ የሆነ ጭቃ(ወልቅ) ስለሚፈጠር ማህበረሰቡ የዕለት ከዕለት ኑሮውን ለመምራት በእጅጉ ይቸገራል፡፡ በዚህም ምክንያት የግብርና ግብዓቶችን ለማቅረብ፣ ህክምና ለማግኘት፣ ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ፣ ገበያ ለመሄድ እና ሌሎች ማህበራዊ ተግባራትን ለማከናወን በጣም ከባድ ነበር፡፡



ወ/ሮ አመለወርቅ

የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ

ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደነበር የቀበሌዉ ሥራ አስኪያጅ ወ/ሮ አመለወርቅ ግዛቸዉ እንደሚከተለዉ ገልፀውታል፡፡ **“እናቶች በወሊድ ወቅት ወደ ጤና ተቋም መሄድ ስለማይችሉ ይሞቱ ነበር፣ በክረምት ወቅት ወደ ገበያ መሄድ ከባድ ነበር፣ እንስሳት በክረምት ወቅት ወደ ህክምና ተቋም መሄድ ስለማይችሉ ይሞቱ ነበር፣ እንስሳት በጭቃ(ወልቅ) እየተያዙ ህይወታቸዉ ያለፍ ነበር፣ በክረምት ሰዉ ሲሞት ለመቅበር እንኳን አዳጋች ነበር፣ ማህበረሰቡ የግብርና ምርት ወደ ገበያ ወስዶ ለመሸጥ ይቸገር ነበር፣** በክረምት ወቅት የምግብ ቀለብ ማዘጋጀት እና ማስፈጨትም ከባድ **ነበር፡፡”**

ሔልቬታስ ኢትዮጵያ የአማራ አካባቢያዊ አስተዳደር ፕሮጀክት በ2011 ዓ.ም ወደአካባቢዉ በመግባት ለተለያዩ አካላት ስለ ተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ የአቅም ግንባታ ስልጠና እና ልምድ ልዉዉጥ እንዲያገኙ በማድረግ ማህበረሰቡ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጣቸዉን የአካባቢያቸዉን ችግሮች በትኩረት ቡድን እንዲለዩ እና በቀበሌዉ ዓመታዊ ዕቅድ ዉስጥ እንዲካተት ተደረገ፡፡ ከዚህም ዉስጥ የጎኛ ጎጥ የመንገድ ችግር የቅድሚያ ቅድሚ እንዲሰጠዉ ከተለዩት ችግሮች ዉስጥ አንዱ ነበር፡፡ ዕቅዱም በቀበሌ ምክር ቤት ፀድቆ ወደ እነማይ ወረዳ ፕላን እና ልማት ቡድን እና መንገድ ጽ/ቤት በመላክ በሴክተሩ ዓመታዊ ዕቅድ ዉስጥ ተካቶ እንዲተገበር ተደረገ፡፡

የአካባቢዉ ማህበረሰብ ችግሩን ለመፍታት በራሳቸዉ ተነሳሽት እና አቅማቸዉን መሰረት በማድረግ ከእያንዳንዱ አባወራ እና እማወራ ከ 400 (አራት መቶ) እስከ 2000 (ሁለት ሺህ) ብር በማዋጣት እና ገንዘብ የማዋጣት አቅም የሌላቸዉ ደግሞ የጉልበት እና የአካባቢ ቁሳቁሶችን በማቅረብ እንዲሁም ከወረዳዉ እና ቀበሌ ምክር ቤት እና መንገድ ጽ/ቤት

በተደረገ የተቀናጀ ክትትል እና ድጋፍ በ2013 ዓ.ም 4 ኪ.ሜትር የጠጠር መንገድ ግንባታ ተጠናቆ ለአገልግሎት በቅቷል፡፡ በመሆኑም የአካባቢዉ ማህበረሰብ መንገድ መጠቀም በመጀመራቸዉ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች መቅረፍ ችለዋል፡፡



ወ/ሮ የኔዉብ፡ የቀበሌዉ ነዋሪ እና የመንገድ ትኩረት ቡድን አባል

የቀበሌዉ ነዋሪ እና የመንገድ ትኩረት ቡድን አባል የሆኑት ወ/ሮ የኔዉብ ደሴ የመንገዱ መሰራት በአካባቢዉ ስላመጣዉ ለዉጥ እንደሚከተለዉ ገልፀዉታል፡፡

**“ከመንገዱ ግንባታ በኋላ አንቡላንስ ወደ ሰፈራችን መምጣት በመቻሉ እና እናቶች ወደ ህክምና ተቋም ሄደዉ መዉለድ ችለዋል፡፡ ባጃጅ፣ ሞተር እና ሚኒባሶች ወደ ጎጡ መግባት በመቻላቸዉ ማህበረሰቡ የትራንስፖርት አገልግሎት ማግኘት ችለዋል፡፡ በተጨማሪም የግብርና ምርቶቻችንን በቀላሉ ወደ ገበያ በማቅረብ በተሻለ ዋጋ በመሸጥ ገቢያችን እንዲሻሻል እገዛ አድርጎልናል፡፡”**

## ▪ ከሴቶችና ስርዓተ ፆታ አኳያ፡

1. የስርዓተፆታ ሀብት ካርታን ትርጉምና ጠቀሜታ መግለጽ

